ሐዋሳ ሪፎርምድ ባፕቲስት ቤተ-ክርስቲያን
Hawassa Reformed Baptist Church

# የዘመን ፍጻሜ

## Eschatology

በመጋቢ ተካልኝ ነ/ሚካኤል

ሐዋሳ ሪፎርምድ ባፕቲስት ቤተ-ክርስቲያን
Hawassa Reformed Baptist Church

# የዘመን ፍጻሜ

# Eschatology

በመጋቢ ተካልኝ ኀ/ሚካኤል

የዘመን ፍጻሜ

© ሚያዚያ 4|2018 ዓ.ም

ጥያቄ አስተያየት ካለዎት

+251906472670 መጋቢ ተካልኝ ሃ/ሚካኤል

የሽፋን ምስል ድዛይን እና የውስጥ ገጽ ቅንብር፥ አቤንኤዘር ዳንኤል

ስልክ፥ +251916698510

ኢሜል፥ abenezeredanielabi@gmail.com

# መቅድም

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት ጥልቅና መሠረታዊ ትምህርቶች መካከል አንዱ ስለ ዘመን ፍጻሜ የሚተነትነው የነገረ ፍጻሜ (Eschatology) ትምህርት ነው። አማኞች ስለሚመጣው ዘመን፣ ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽዓትና ስለ ፍጥረት ሁሉ መደምደሚያ ግልጽ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ የክርስቲያን ሕይወት ተስፋን መሠረት ለማስያዝ እጅግ አስፈላጊ ነው።

ይህ አሁን በእጃችሁ የሚገኘው የጽሑፍ ሰነድ፣ በHawassa Reformed Baptist Church በመጋቢ ተካልኝ ኃይለሚካኤል አማካኝነት ለተከታታይ ስድስት ሳምንታት ሲሰጥ የነበረው የነገረ ፍጻሜ ትምህርት ስብስብ ነው። ትምህርቱ በመጋቢው አማካኝነት በቤተክርስቲያኗ ውስጥ በነበረው የትምህርት ጊዜ የቀረበ(የተማሩት ትምህርት) ቢሆንም፣ ለብዙዎች ይበልጥ ተደራሽ እንዲሆን፣ በጥልቀት ለማጥናት እንዲመችና ለትውልድ እንዲቀመጥ ታስቦ በጽሑፍ ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

በትምህርቱ ውስጥ ስለ ሺኛው ዓመት መንግሥት የሚነሱ የተለያዩ አመለካከቶች (Premillennialism, Postmillennialism, Amillennialism እና Preterism)፣ የዘመን ፍጻሜ ምልክቶችና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢቶች በመጋቢ ተካልኝ ሰፊ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል።

ይህ የጽሑፍ ትምህርት፣ በድምፅ ሲሰጥ የነበረውን መንፈሳዊ ይዘት ሳይለቅ የቀረበ ሲሆን፣ እያንዳንዱ አንባቢ የዘመኑን ፍጻሜ መረዳት እንዲችልና ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ራሱን እንዲያዘጋጅ ትልቅ እገዛ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል።

መልካም ንባብ!



GFX By: AD Graphics | +251916698510

በወንድም ተክሌ ኃ/ሚካኤል

# መግቢያ

ነገረ ፍፃሜ በእግዚአብሔር የማዳን እቅድ ውስጥ ያሉትን “የመጨረሻ ነገሮች” ወይም የመጨረሻ ክስተቶችን የሚያጠና የስነ-መለኮት ክፍል ነው። በክርስቲያናዊ ሥነ-መለኮት ውስጥ ፣ ነገረ ፍፃሜ እንደ ሞት ፣ ፍርድ ፣ መንግስተ ሰማያት ፣ ሲኦል ፣ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ፣ የሙታን ትንሳኤ እና የፍጥረት መታደስ ያሉ ጭብጦችን ይዳስሳል። በወደፊት ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ቢሆንም ፣ መላምት ብቻ ግን አይደለም። ይልቁንም አማኞች የአሁንን ጊዜ እንዴት እንደሚረዱ እና በተስፋ እንዲኖሩ የሚያስተምር የክርስትና እምነት ወሳኝ ክፍል ነው።

ከቅዱሳት መጻሕፍት መጀመሪያ አንስቶ እስከ መደምደሚያው ድረስ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ግቡ እንዴት እንደሚሄድ ያብራራል።  በዘፍጥረት ውስጥ ያለው የፍጥረት ታሪክ በእግዚአብሔር የተፈጠረውን መልካም ዓለም ያስተዋውቃል ፣ ነገር ግን በኃጢአት ምክንያት ፍጥረት ወደ ጥፋት እና ፍርድ ስር ሲወድቅ እንመለከታለን።  የቀረው የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ በታሪክ ውስጥ እንዴት እንደተገለጠ ይነግረናል። በክርስቶስ የመጨረሻ ድል እና የሁሉንም ነገር ወደ ነበረበት መመለስን እና ወደ ተሻለው ግብ እንደሚመጣ ይነግረናል። ይህ ገጽታ ለክርስቲያኖች እምነት ጠንካራ የዓላማ እና የቆራጥነት ስሜትን ይፈጥራል።

በብሉይ ኪዳን የፍጻሜ ዘመን ተስፋ እግዚአብሔር ለእስራኤል ከሰጠው ተስፋ ጋር ተያይዞ ብዙ ጊዜ ይገለጻል። ነቢያት ስለሚመጣው “የእግዚአብሔር ቀን” እግዚአብሔር በክፋት ላይ የሚፈርድበት፣ ሕዝቡን የሚያጸድቅበት እና ጽድቅን የሚያቆምበት ጊዜ ይናገራል። እንደ ኢሳይያስ፣ ሕዝቅኤል እና ዳንኤል ባሉ መጻሕፍት ውስጥ ያሉ ምንባቦች የወደፊቱን ተሃድሶ ፣ ትንሣኤ እና የእግዚአብሔርን መንግሥት ይገልጻሉ። እነዚህ ተስፋዎች አንዳንድ ጊዜ ወዲያውኑ ከታሪካዊ ክንውኖች ጋር የተገናኙ ነበሩ ፣ ነገር ግን ከእነሱ ባሻገር ወደ ታላቅ ፍጻሜ ያመለክታሉ።

ስለ መሲሑ ተስፋ ፣ መዳንና ሰላምን የሚያመጣ የተቀባ ንጉሥ እስራኤል በተስፋ በሚጠብቁት ነገር ውስጥ ዋነኛው ነበር።

አዲስ ኪዳን ኢየሱስ ክርስቶስን የእነዚህ ተስፋዎች ፍጻሜ አድርጎ ያቀርባል። በክርስቶስ መምጣት፣ “የመጨረሻው ቀን” ወሳኝ በሆነ መንገድ መጀመሩን ያብራራል። ሆኖም የአዲስ ኪዳን ታሪክ ሙሉ በመሉ እንዳልተፈፀመ ያስተምራል። የነገረ መለኮት ሊቃውንት ብዙውን ጊዜ “already and not yet” ብለው ይጠሩታል። የእግዚአብሔር መንግሥት በክርስቶስ ተከፍታለች ፣ ነገር ግን ገና ሙሉ በሙሉ አልተጠናቀቀችም። የዘመን ፍፃሜ ትምህርት አሁን ያለውን እውነታ እና የወደፊት ተስፋን አንድ ላይ ይይዛል። መጽሐፍ ቅዱሳችን በመጨረሻ ሊሆን ስላለው ነገር በተመለከተ ችላ እንዳንል ይነግረናል። በመሆኑም ክርስቲያኖች በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጹትን እውነታዎች በጥንቃቄ በመመልከት የተነገሩትን ተስፋዎች መጠባበቅና የቃሉ ያልተፋታ የቋም ሊኖራቸው ይስፈልጋል።


GFX By: AD Graphics | +251916698510

HAWASSA REFORMED Baptist Church HRBC

# የዘመን ፍፃሜ - Eschatology -

በወንጌላዊ ተስፋዬ ኃ/ሚካኤል

ስለፍጥረት አጀማመር፣ ስለነበረው ሂደት ሁላችንም እናውቃለን። ነገርግን የፍጥረት መጨረሻውን በተመለከተ ክርስቶስ እንደሚመጣ ከማወቅ ባለፈ ስለመጨረሻው ዘመን ብዙ ሰው ትኩረት የሚሰጠው አይመስለኝም። በሁለት ምክንያቶች የዘመን መጨረሻን መረዳት በጣም ከባድ እና ሰፊ ነገር እንደሆነ በማሰብ ወይም የዘመን መጨረሻን ባላውቅም ችግር የለውም ብሎ በማሰብ ሊሆን ይችላል። ከእዚህ የተነሳ ስለዘመን ፍፃሜ ብዙ ሰው ግንዛቤው ሳይኖረው ይቀራል።

## ይህንን ትምህርት ስንጀምር የምንመለከታቸው መሰረታዊ ነገሮች፦

<u>ስለ ሺኛው መንግስት፦</u> ከሺኛው መንግስት ጋር በተያያዘ ሶስት ዋና ዋና ምልከታዎች አሉ።

1ኛ| Premillennialism ቅድመ ሺ አመት (ከሺው አመት መንግስት በፊት ክርስቶስ ቀድሞ ይመጣል።)

2ኛ| Postmillennialism ድህረ ሺ አመት (ከሺው አመት መንግስት በኋላ ክርስቶስ ይመጣል።)

3ኛ| Amillennialism አልቦ ሺ አመት (የሺኛው መንግስት አመት አፈፃፀም በምድራዊ መንግስት ሳይሆን አሁን ባለው በክርስቶስ መንፈሳዊ መንግስት ነው።

#Preterism (Full Preterism እና Partial Preterism)

- Full Preterism ሁሉም መፅሐፍ ቅዱስ ላይ የተነገሩ ትንቢቶች በ 70 AD ተፈፅመዋል የሚል ሲሆን ለወደፊት የምንጠብቀው የክርስቶስ ዳግም ምፅአት፣ የሞተ ሰዎች አካላዊ ትንሣኤ የመጨረሻው ፍርድ የለም ብለው ያምናሉ።

- Partial Preterism ደሞ አብዛኛው ትንቢቶች በ 70 AD ተፈፅመዋል፤ ያልተፈፀሙ ትንቢቶች አሉ። የክርስቶስ አካላዊ መምጣት፣ የሞተ ሰዎች አካላዊ ትንሣኤ፣ የመጨረሻ ፍርድ እንዲሁም አንድ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር አሁንም ይመጣሉ ብለው ያምናሉ።

**የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፦** ማቴ 24 እና 25 ፣ ሮሜ 9-11 ዳሰሳ(እስራኤል ሁሉ ይድናል የሚለውን) ፣ ራዕይ 20 ፣ እንዲሁም የተሰሎንቄን መፅሐፍ የምንመለከት ይሆናል *Postmillennialism

- ## ስለ ዘመን ፍፃሜ ማወቅ ለምን አስፈላጊ ሆነ?

1ኛ| የዘመን ፍፃሜን በተመለከተ ignorant እንዳንሆን መፅሐፍ ቅዱስ በቀጥታ ትዕዛዝ ስለሚሰጠን።

1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 4:13

13 ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ፥ አንቀላፍተው ስላሉት ታውቁ ዘንድ እንወዳለን።

አማርኛው ለመተርጎም አስቸጋሪ ስለሆነ positive አድርጎ ነው ያስቀመጠው። የግርከኛውን ከተመለከትን አላዋቂ(Ignorant or Uninformed) እንድትሆኑ አንፈልግም። ጳውሎስ የዘመን ፍፃሜን አለማወቅ የማልታገሰው ጉዳይ ነው እያለ ነው። የመጨረሻውን ዘመን በተመለከተ ከባድ ነው፣ ስደርስ አየዋለሁ በማለት ወደ ጎን ይደረጋል። ጳውሎስ ደግሞ የዘመን ፍፃሜን ጉዳይ በተመለከተ አላዋቂዎች እንድትሆኑ አልፈልግም ይላል።

2ኛ| ጌታ ኢየሱስ አይመጣም የሚሉ የስህተት ትምህርቶች ስላሉ እንነሱን ለመከላከል።

ቻርለስ ራስል Jehovah's Witnesses መሪ ኢየሱስ በ1914 ዓ.ም ይመጣል ብሎ ትንቢት ተናግሮ ነበር። ኢየሱስ እንዳልመጣ ሲታወቅ ሰዎች ቻርለስ ራስልን ጠየቁት። እርሱም ኢየሱስ በሚስጥር መጥቶ ሄዷል አለ። አስተማሪዎች የነበሩት በእኛ ዘመን ብቻ አይደሉም ያሉት። በእነጴጥሮስ ዘመንም ነበሩ።

2ኛ የጴጥሮስ መልእክት 3:3-4

3 ከሁሉ አስቀድሞ ይህን ዕወቁ፤ በመጨረሻው ዘመን የራሳቸውን ክፉ ምኞት የሚከተሉ ዘባቾች እየዘበቱ ይመጣሉ። 4 እነርሱም፣ “ ‘እመጣለሁ’ ያለው ታዲያ የት



GFX By: AD Graphics | +251916698510

አለ? አባቶች ከሞቱበት ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥቶ
እስካሁን ድረስ ሁሉም ነገር እንዳለ ይኖራል" ይላሉ፡፡

እንዲሁም ክርስቶስ በበዓለ ኀምሳ መጥቷል የሚሉ አሉ፡፡ ነገርግን ስለክርስቶስ ዳግም መምጣት ከበዓለ ኀምሳ በኋላም ተነግሯል፡፡
ለምሳሌ፦ ዕብ 9:28 ፤ ራዕ 1:7 ኢየሱስ የዘገየ ይመስለናል ነገር ግን እስራኤላውያን ኢየሱስ ይወለዳል ብለው የጠበቁትን ያህል እንኳን አልጠበቅንም፡፡

3ኛ| Eschatology ለእኛ ትልቅ እና ፅኑ ተስፋችን ስለሆነ፡፡

ፊልጵስዩስ 3 (አዲሱ መ.ት)

20 እኛ ግን አገራችን በሰማይ ነው፤ ከዚያ የሚመጣውንም
አዳኝ፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በናፍቆት እንጠባበቃለን፤
21 እርሱም ሁሉን ለራሱ ባስገዛበት ኀይል፣ ክቡር ሥጋውን
እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል፡፡

4ኛ| ሁሉን ነገር ትተን ሀሳባዊያን ሆነን እየሱስን መጠበቅ ሳይሆን በምግባሪያዊ ህይወት ራሱን እየጠበቀ መኖር ስላለብን ነው፡፡

ሉቃስ 12 ላይ ጌታ ኢየሱስ አንድ መኮንን መንግስት ይዞ ሊመጣ ሩቅ ሀገር ሄዶ ይላል፡፡ ከእዛ ሁለት ሰዎችን እንደ ምሳሌ ያቀርባል፡፡ 1ኛው, ትጉ ባሪያ ነው፣ ሌላኛው ደግሞ ሀኬተኛ ባሪያ ነው፡፡ ለእነዚህ አደራ ይሰጣቸዋል ቤቴን ተቆጣጠሩልኝ ይላቸዋል፡፡ ትጉው ባሪያ፦ ጌታዬ መቼ እንደሚመጣ አላውቅም ብሎ ኑሮውን እና ምግባሩን ከመምጣቱ ጋር አያይዞ የሚኖር፣ የቤቱን ሰዎች በአግባቡ የሚመግብ ነው፡፡ ጌታዬ ይመጣል በሚል ልብ ነበር ሲጠብቅ የነበረው፡፡

ታካቹ ሰው ደግሞ ጌታዬ ይመጣል ብሎ ልቡ አይንተከተክም፡፡ ይዘገያል ብሎ ፊታ እያለ ነበር፡፡ ያው መቼም አይመጣም ብሎ አያስብም፡፡ ነገር ግን የመምጣቱ ሁኔታ ልቡ ውስጥ የለም፣ ዝም ብሎ የእራሱን ኑሮ ነው የሚኖረው፡፡

## ▪ ESCHATOLOGY ምንድነው?

ከቃሉ ብንጀምር **ፍፃሜ** የሚል ትርጉም ካለው ኤስካቶስ/eschatos ከሚል የግሪክ ቃል የተወሰደ ነው፡፡ የመጨረሻዎቹ ነገሮች ጥናት ማለት ነው(ከክርስቶስ ዳግም ምፅአት ጋር የተያያዘ)

የዘመን ፍፃሜን ማለት የአለም ፍፃሜ ማለት አይደለም፡፡ በእርግጥ የዘመን ፍፃሜ የሚለው እና የአለም ፍፃሜ የሚለውን የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች በተለዋዋጭነት ይጠቀሙታል፡፡ ለምሳሌ፦

የማቴዎስ ወንጌል 24:3

3በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ተቀምጦ ሳለ፣ ደቀ መዛሙርቱ
ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው "እስቲ ንገረን፤ የምትለው
ሁሉ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ
ምልክትስ ምንድን ነው?" አሉት፡፡

እዚህ ጋር አለም የሚለው ቃል ኮስሞስ ሳይሆን aion ነው፡፡ ይህ ማለት ዘመን(age) ማለት ነው፡፡ አንድም ቦታ መፅሐፍ ቅዱስ ስለ አለምፍፃሜ ሲናገር ስለ ቁሳዊው አለም መወገድ አይናገርም፡፡ የሚወገደው በዘመን ውስጥ ስላለው ስርአት ነው፡፡ ስለዚህ የአለም መጨረሻ ማለት የሰማይና የምድር መጥፊያ ማለት አይደለም፡፡ ሰማይና ምድር ይታደሳሉ እንጂ አይጠፉም፡፡ ለምሳሌ ፦

2ኛ የጴጥሮስ መልእክት 3:6-7

6 በዚያን ጊዜ የነበረው ዓለም በውሃ ተጥለቅልቆ ጠፋ፡፡
7 በዚያው ቃል ደግሞ አሁን ያሉት ሰማያትና ምድር፣
ኃጢአተኞች እስከሚጠፉበት እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ለእሳት
ተጠብቀዋል፡፡

አሮጌው ስርአት አልፎ አዲስ ስርአት ነው የሚመጣው፡፡ እግዚአብሔር የፈጠረውን አለም በኃጢአት ምክንያት ካጠፋው ተሸናፊ ነው፡፡ ይህ አለም


GFX By: AD Graphics | +251916698510

ፍፃሜ የለውም ይቀጥላል። ሥርአቱ(system) ነው የሚቀየረው።

## • ታዲያ የዘመን መጨረሻ ስንል ስለየትኛው ዘመን ነው እያወራን ያለነው?

ዘመንን በተመለከተ እስራኤላውያን በሁለት ነው የሚከፍሉት። የሙሴ ዘመን እና የመሲሁ ዘመን (Olam HaZeh & Olam HaBa) የሙሴ ዘመን በክርስቶስ መምጣት ተጠናቋል። ለምሳሌ ሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 ከተመለከትን በኢዩል መፅሐፍ የተነገረውን አሁን ተፈፀመ ይለናል። በኢዮኤል መፅሐፍ ስለመጨረሻው ዘመን ይናገራል። ያ የመጨረሻው ዘመን የሙሴ ዘመን ማብቃቱን ነው የሚናገረው። የመሲሁ ዘመን በይፋ መጀመሩን የመለክታል።

**ገላትያ 4:4**

4 ነገር ግን <u>የዘመኑ ፍጻሜ</u> በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤

ይህ የሙሴ ዘመን ተጠናቆ የክርስቶስ ዘመን መጀመሩን የሚያመለክት ነው።

**ኤፌሶን 1:10**

10 <u>በዘመን ፍጻሜ</u> ይሆን ዘንድ ያለው ሐሳቡ፣ በሰማይም በምድርም ያሉትን ነገሮች ሁሉ ራስ በሆነው በክርስቶስ ሥር ለመጠቅለል ነው።

ይህ የመሲሁ ዘመን በሙላት ተገልጦ ፍፃሜውን ሲያገኝ ማለት ነው። የመሲሁ ዘመን በሙላት የሚገለጥበት ኃጢአት እና ኃጢአተኞች የሚወገዱበትን ዘመን ይመጣል።

# • PREMILLENNIALISM ምንድነው?

ይህ ምልከታ ሁለት ክፍሎች አሉት።
1ኛው, Historic premillennialism ሲሆን፣
2ኛው, dispensational premillennialism ናቸው።

## 1| <u>Historic Premillennialism</u>

ቤተክርስቲያን እና አይሁድን ለሁለት ነጥሎ የማየይ አመለካከት ሲሆን ቤተክርስቲያን ከብሉይ ኪዳን እስራኤል እንደቀጠለች፣ ቤተክርስቲያን የእስራኤልን ኪዳን ወራሽ እንደሆነች የሚያስተምር ምልከታ ነው። ወይንም Replacement Theology ማለት እንችላለን።

ቤተክርስቲያን በታላቁ መከራ ታልፋለች፣ ከእዚያም ኢየሱስ ከመላዕክት ጋር በክብር ይገለጣል። የሞቱ ቅዱሳን ከሙታን ይቀሰቅሳሉ፣ በህይወት ያሉትም ጌታቸውን ለመቀበል ወደ ሰማይ ይነጠቃሉ፣ ይለወጣሉም። ከእዚያም በክብር ከኢየሱስ ጋር ይመለሳሉ ፣ ለአንድ ሺ አመት ከኢየሱስ ጋር ይነግሳሉ።

## 2| <u>Dispensational Premillennialism</u>

ቤተክርስቲያን እና እስራኤል ፈፅሞ የተለያዩ ሁለት የእግዚአብሔር ህዝቦች ናቸዉ፣ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የገባውን ምድራዊ ኪዳን አቋርጦል፣ ቤተክርስቲያን እስራኤልን አልተካችም የሚል አስተምህሮ ነው።

ከሰባቱ አመት መከራ በፊት ኢየሱስ በስውር ይመጣል፥ ቅዱሳንን ከሞት ይቀሰቅሳል፣ ከእዚያ ቤተክርስቲያን ትነጠቃለች። በሰባት አመት በሰማይ የበጉ እና የቤተክርስቲያን ሰርግ ይሆናል፣ በምድር ላይ ደግሞ አውሬው ይነግሳል፥ ከእስራኤልም ጋር ቤተመቅደስ ለመስራት ቃልኪዳን ይገባል።

ከእዚያም ለሶስት አመት ተኩል ሰላም ይሆናል፤ በቤተመቅሱ ጣኦት ያቆማል፣ በምድር ላይ ታላቅ መከራ ይሆናል፣ እስራኤልን አጥብቆ ያስጨንቃል።



GFX By: AD Graphics | +251916698510

የአርማ ጌዲዮን ጦርነት በእስራኤል እና በተቀረው አለም መካከል ያደርጋል፡፡ በእዚህ የጭንቅ ጊዜ እስራኤልን ለመታደግ ኢየሱስ በመላዕክት ታጅቦ ከሰማይ ይገለጣል፡፡ ከቤተክርስቲያን ጋር ከሰማይ ይወርዳል፣ የእስራኤልን ጠላቶች ይመታል፣ በምድርም የአንድ ሺ መንግስት ይመሰርታል፡፡

**በሌላ አገላለጽ ፦**

ከመሱሁ ሞት በኋላ መፈፀም በነበረበት 1 ሱባኤ መካከል በዳንኤል መፅሐፍ ያልተመዘገበ የቤተክርስቲያን ዘመን ጣልቃ ገባ ይላሉ፡፡ ይህንን የቤተክርስቲያን ዘመን በማቴዎስ ወንጌል 21:43 መሰረት ያብራሩታል፡፡

ማቴዎስ ወንጌል 21:43

43 “ስለዚህ እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ከእናንተ ተወስዳ ፍሬዋን ለሚያፈራ ሕዝብ ትሰጣለች፤

የቤተክርስቲያን ዘመን የጀመረው ከጴንጠቆስጤ ቀን ጀምሮ ነው፣ የቤተክርስቲያን ዘመን ፍፃሜ በሮሜ 11 መሰረት የአህዛብ ሙላት ነው ይላሉ፡፡ የቤተክርስቲያን ዘመን እንደተጠናቀቀ ጌታ በድንገት እንደ ሌባ ይመጣል፡፡ በድንገት መምጣቱ በስውር አማኞችን ለመውሰድ መምጣቱን የሚያመለክት ነው ይላሉ፡፡ በእዚህ ጊዜ የሞቱ ሰዎች ትንሳኤአቸውን ያገኛሉ፡፡ ይህ በዮሐንስ ራዕይ 20:5 ላይ የመጀመሪያው ትንሳኤ ነው ተብሎ የተገለጸው፡፡ 1ኛ ተሰሎንቄ 4:15-17 ላይ የአማኞችን ትንሳኤ ከክርስቶስ ምፅአት ጋር አያይዞ ይጠቀማል፡፡ ዳግሞም በህይወት ያሉቱም ይነጠቃሉ፡፡ ከእዚህ በኋላ 7ቱ የመከራ አመት ይጀምራል፡፡ ቤተክርስቲያን ከተነጠቀች በኋላ ኢየሱስ በሰማይ ለእያንዳንዱ እንደየስራው ይሸልማቸዋል፡፡ በምድር ላይ ግን በእዚህ የተሰባቱ አመት የመከራ ጊዜ ሰይጣን ይነግሳል፡፡ በምድር ላይ ሰይጣን የሚነግስበት ምክንያት ቤተክርስቲያን በምድር ስለሌለች ነው፡፡ ይህ በዳንኤል መፅሐፍ ተቋርጦ የነበረው 70ኛው ሱባኤ ነው፡፡ ይህ ነው የዲስፔንሴሽናሊዝም አስተምህሮ፡፡

## ▪ የቤተክርስቲያን ንጥቀት/RAPTURE

በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የንጥቀት ትምህርት የጀመረው ከ150 አመት በፊት በ19ኛው መቶ ክፍለዘመን ነው፡፡ John Nelson Darby የሚባል በእንግሊዝ አገር ውስጥ የሚኖር ሰው ያስፋፋው ትምህርት ነው፡፡ ከዚያ በፊት በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ አይታወቅም ነበር፡፡ አማኞች ንጥቀት የሚባል ነገር አያውቁም፡፡ ጌታ ኢየሱስ አንዴ ነው የሚመጣው፣ ለፍርድ ነው የሚመጣው የሚል አስተሳሰብ ነበር የነበረው፡፡

**ዋናው ነገር ደሞ፦** ትምህርቱ አዲስ ነው? የቆየ ነው? ከሚለውም ባለፈ መፅሐፍ ቅዱሳዊ ነው? ወይንስ አይደለም የሚውን መመልከት አለብን፡፡

በመጀመሪያ ይህ ትምህርት በአንድ ጥቅስ ላይ የተመሰረተ ትምህርት ነው፡፡ ስለዘመን ፍፃሜ በዝርዝር የሚያወሩ በርካታ የመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርት ኖሮ ስለ ንጥቀት ቀን አንድ የመፅሐፍ ወቅዱስ text ላይ ብቻ እንዴት ሊኖር ቻለ?

1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 4:15-17

15 በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህን ነው፤ እኛ በሕይወት ያለንና
ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉትን አንቀድምም፤
16 ጌታ ራሱ በታላቅ ትእዛዝ፣ በመላእክት አለቃ ድምፅና
በእግዚአብሔር የመለከት ድምፅ ከሰማይ ይወርዳልና፡፡
በክርስቶስ የሞቱትም አስቀድመው ይነሣሉ፡፡
17 ከዚያም
በኋላ እኛ የቀረነው፣ በሕይወትም የምንኖረው ጌታን
በአየር ላይ ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤
በዚህም መሠረት ለዘላለም ከጌታ ጋር እንሆናለን፡፡

ይህንን ክፍል ከማብራራቴ አስቀድሞ በመጀመሪያ ይህ የንጥቀ ትምህርት የክርስቶስ ትምህርት እና የሐዋሪያቱ ትምህርት እንዳልሆነ እንመልከት፡፡

2ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2:1-4

1 ወንድሞች ሆይ፤ ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ


GFX By: AD Graphics | +251916698510

መምጣትና ወደ እርሱም ስለ መሰብሰባችን ይህን እንለምናችኋለን፤ 2 በመንፈስ ወይም በቃል ወይም ከእኛ እንደ ተላከ መልእክት የጌታ ቀን ደርሷል ብላችሁ ፈጥናችሁ ከአእምሮቻችሁ አትናወጡ፤ አትደንግጡም።

የተሰሎንቄ ሰዎች የጌታ ቀን ደርሷል ብለው ታውከዋል። ጳውሎስ እነዚህን ሰዎች የጌታ ቀን መጥቷል ብላችሁ አትናወጡ፣ አትደንግጡ ይላቸዋል። እዚህ ጋር ግን አንድ ጥያቄ እንጠይቅ። ሐዋሪያቱ አስቀድሞ ቤተክርስቲያን ከሰባቱ አመት መከራ በኋላ ትነጠቃለች የሚል አስተምህሮ ከነበራቸው እነዚህ የተሰሎንቄ ሰዎች የጌታ ቀን ደርሷል ብለው ምን ያስደነግጣቸዋል?መሆን የነበረበት ጌታ መጥቶ ይወስደናል፣ ለ7 አመትም በአየር ላይ ከእርሱ ጋር እንኖራለን ብለው ነበር መደሰት የነበረባቸው። በጣም የሚገርመው ደሞ ወደታች ሲመጣ ስለ ዘመን ፍፃሜ አስቀድሞ ተናግሮ ነበር።

2ኛ ተሰሎንቄ 2:5-8

5 ከእናንተ ጋር በነበርሁበት ጊዜ፣ እነዚህን ነገሮች ነግሬአችሁ እንደ ነበር ትዝ አይላችሁምን? 6 በራሱ ጊዜ ይገለጥ ዘንድ አሁን ምን እንደሚከለክለው ታውቃላችሁ። 7 የዐመፅ ምስጢር አሁንም እንኳ እየሠራ ነውና፤ ነገር ግን ይህ የሚሆነው የሚከለክለው ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ ብቻ ነው 8 ከዚያም በኋላ ጌታ ኢየሱስ በአፉ እስትንፋስ የሚያስወግደውና በምጽአቱም ክብር ፈጽሞ የሚያጠፋው ዐመፀኛ ይገለጣል።

ስለ ቤተክርስቲያን ንጥቀት አስቀድሞ ከነገራቸው እንዴት ክርስቶስ ይመጣል ብለው ይደነግጣሉ?

የ1ኛ, ተሰሎንቄን 4:1

**1ኛ|** ኢየሱስ በስውር መጥቶ ቤተክርስቲያንን አይወስዳትም።

- ቁጥር 16 16 ጌታ ራሱ በታላቅ ትእዛዝ፣ በመላእክት አለቃ ድምፅና በእግዚአብሔር የመለከት ድምፅ ከሰማይ ይወርዳልና።

ኢየሱስ እዚህ ጋር ሲመጣ ሹልክ ብሎ መጥቶ ማንም ሳያየውም ቤተክርስቲያንን ይዞ የሚሄድ እንዳልሆነ ያስረዳናል በስውር የሆነን አመጣጥ አይገልጽም።

ሶስት ቃላቶችን በመሰረታዊነት እንመልከት :"ጌታ ራሱ በታላቅ ትእዛዝ" ይህ ከፍተኛ ትዕዛዝን የሚያመለክት ነው÷ "በመላእክት አለቃ ድምፅ" እና በእግዚአብሔር የመለከት ድምፅ÷ ይህ የመለከት ድምፅ የድል ድምፅ ነው እግዚአብሔር ህዝቡን ሊያድን እንደመጣ ጠላቶቹን ለመበቀል እንደመጣ የሚታወጅ ድምፅ ነው። የድል ድምፅ በስውር ሊሆን አይችልም ስለዚህ የኢየሱስ አመጣጥ የስውር ሊሆን አይደለም።

በድብቅ መጥቶ በስውር ቤተክርስቲያንን ይወስዳታል የሚለው ትምህርት ከየት የመጣ ነው? **መፅሐፍ የሚለው የወጉት ሁሉ ያዩታል ነው የሚለው።**

**2ኛ|** በአየር ላይ እንነጠቃለን ሲል፦ በአየር ላይ ተንሳፈን እንቀራለን እያለ አያደለም፣ ደግሞም ወደሰማይ እንሄዳለን እያለ አይደለም።

የተሰሎንቄ ከተማ አንድ ጌታ ወይንም ንጉስ በአመት አንዴ መጥቶ የሚጎበኛት ከተማ ነች። በቄሳር ይጎበኛታል ወይንም ለቄሳር የቀረቡ የከበሩ ሰዎች ትጎበኛለች። ጌታው ለጉብኝት ወደከተማው በሚወርድበት ጊዜ፣ በወታደሮችን ታጅቦ ይመጣል፣ ወታደሮችም መለከት ይነፋሉ፣ ህዝቡንም ልትቀበሉት ውጡ የሚል ድምፅ ያሰማሉ። ህዝቡም ከከተማው ወጥተው ይቀበሉትና ንጉሱን ወደ ከተማው ያስገቡታ።

ስለዚህ የተሰሎንቄ ሰዎች ጳውሎስ ምን እያወራ እንደሆነ ለመረዳት አይከብዳቸውም።

እዚህ ጋር **<u>ጌታን ለመቀበል</u>** ነው የሚለው እንጂ እና ሊወስድ አይደለም የሚመጣው። ነገስታቶችም ድልአድርገው ሲመለሱ ህዝቡ ከከተማው ወጥቶ ንጉሱን ይቀቡ እና ወደ ከተማው ይዘውት ያስገቡታል። ስለዚህ ንጥቀት Figurative speech እንጂ literal አይደለም።

## “በአየር ላይ”

ኤፌሶን 2:2

> 2 በዚህም፣ የዓለምን ክፉ መንገድ ተከትላችሁ፣ በአየር ላይ ላሉት መንፈሳውያን ኀይላት ገዥ ለሆነውና አሁንም ለእግዚአብሔር በማይታዘዙት ሰዎች ላይ ለሚሠራው መንፈስ እየታዘዛችሁ ትኖሩ ነበር።

አየር የሚለው የምናውቀውን አይር አይደለም። ተሰሎንቄ ላይ ያለው **Spiritual realm/መንፈሳዊ ስልጣንን** የሚያመለክት ነው። በአየር ላይ የሚለውን አንዳንድ ምሁራን እንደሚሉት፦ በኤፌሶን መፅሐፍ ላይ በአየር ላይ የሚሰራ፣ የሚሰለጥን የመንፈስ ሀለቃ ነበር። ይህ በክርስቶስ መምጣት ድል መደረጉን እና ይህ የአየር ስፍራ አሁን ነፃ መሆኑን እያመለከተ ነው።

## “ደመና”

የእግዚአብሔርን መገኘት፣ ግርማ እና ክብርን የሚወክል ነው። የእግዚአብሔር ክብር፣ መገኘት በሞላበት ነው ኢየሱስን የሚቀበሉት እያለ ነው። ከእዚያስ? ቀጥር 17 ሲጨርስ፦ **በዚህም መሠረት ለዘላለም ከጌታ ጋር እንሆናለን።**

ሌላኛው የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚጠቀሙት፦

1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 15:51-52

> 51 እነሆ፤ አንድ ምስጢር እነግራችኋለሁ፤ ሁላችን
> አናንቀላፋም፤ ነገር ግን ሁላችንም እንለወጣለን፤ 52 ይህም
> የሚሆነው የመጨረሻው መለከት ሲነፋ ድንገት በቅጽበተ
> ዐይን ነው። መለከት ይነፋል፤ ሙታን የማይበሰብሱ ሆነው
> ይነሣሉ፤ እኛም እንለወጣለን።

እዚህ ጋር ስለመነጠቅ አያወራም፣ መነጠቅ እና መለወጥ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። እና እንለወጣለን እንጂ የሚለው እንነጠቃለን አይደለም የሚለው።

## የDISPENSATIONAL ስህተቶች፦

1. መፅሐፍ ቅዱስን በኪዳናት ሳይሆን በዘመናት ከፋፍለው ነው የሚተረጉሙት።
2. የትንቢት አተረጓጎምን በተመለከተ በጥሬው/ቀጥታ (Literal Prophecy interpretation) ነውየሚከተሉት።
3. በከፋፈሉበት የዘመን ልክ የድነት መንገዱም የተለያየ ነው። በመንግቱ ወንጌል ጊዜ ሰው የሚድንበት መንገድና በፀጋው ወንጌል ዘመን ሰው የሚድንበት መንገድ የተለያየ ነው። በህግ ዘመን እና በፀጋ ዘመን የሚድኑበትን መንገድ የተለያየ ነው። ወዘተረፈ
4. ሐዋርያቱ እና ክርስቶስ የሰበኩት የእግዚአብሔርን መንግስት ወንጌል ሲሆን ጳውሎስ የሰበከው የጸጋ ወንጌልን ነው።
5. ለቤተ ክርስትያን የሚሆነውን መገለጥ የተቀበለው ጳውሎስ ነው።
6. እግዚአብሔር ሁለት ህዝብ ሁለት አለማ ነው ያለው። እስራኤል የእግዚአብሔር ሕዝብ ስትሆን ቤተ ክርስትያን ግን የክርስቶስ አካል ናት። ለእስራኤል ያለው አላማ እና ለቤተክርስቲያን ያለው አላማ የተለያየ ነው።
7. በዲስፐንሴሽናሊዝም የእግዚአብሔር መንግስት እና መንግስተ ሰማያት ይለያያሉ። መንግስተ ሰማያት ለእስራኤል ሊሰጥ የነበረው መሲሃዊው መንግስት ሲሆን እስራኤል ስላልተቀበለችው እና መሲሁን ስለሰቀለች ለሺው ዓመት ተላልፏል።



GFX By: AD Graphics | +251916698510

# መነጠቅ ወይንስ መንጠቅ?

የ1ኛ ተሰሎንቄ 4:17 ሃሳብ ንጥቅ ብሎ ስለመሄድ አያወራም። መፅሐፍ ቅዱስ ላይ ያለው መነጠቅ ሳይሆን መንጠቅ ነው። ተሰሎንቄ ላይ የተጠቀሰው ቃል (ἁρπαγησόμεθα) **<u>ሀርፓጌሳማታ</u>** ነው የሚለው የግሪኩ ቃል፦ ነጥቆ ለእራስ ማድረግ ወይንም ዘርፎ ለእራስ ማድረግ ማለት ነው (Snatched away)

ማቴዎስ 13፥19 (አዲሱ መ.ት)

> የእግዚአብሔርን መንግሥት ቃል ሰምቶ ከማያስተውል ከማንኛውም ሰው ልብ ውስጥ ክፉው መጥቶ የተዘራውን ዘር ይነጥቃል።

ዮሐንስ 10፥28 (አዲሱ መ.ት)

> “እኔ የዘላለም ሕይወት እሰጣቸዋለሁ፤ ከቶ አይጠፉም፤ ከእጄም ሊነጥቃቸው የሚችል ማንም የለም።”

ሐዋርያት 8፥39 (አዲሱ መ.ት)

> “ከውሃውም በወጡ ጊዜ፣ የጌታ መንፈስ ፊልጶስን ነጥቆ ወሰደው፤

ሐዋርያት 23፥10 (አዲሱ መ.ት)

> “ጠቡ ከማየሉ የተነሣም አዛዡ ጳውሎስን እንዳይገነጣጥሉት ፈራ፤ ስለዚህ ወታደሮቹ ወርደው ከመካከላቸው ነጥቀው ወደ ጦሩ ሰፈር እንዲያስገቡት አዘዘ።”

ይሁዳ 1፥23 (አዲሱ መ.ት)

> “አንዳንዶችን ከእሳት ነጥቃችሁ አድኗቸው፤

ምንድነው የምንነጥቀው? የተዘጋጀልንን መንግስት የእራሳችን እናደርጋለን።

የማቴዎስ ወንጌል 11:12

> 12 ከመጥምቁም ከዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ መንግሥተ ሰማያት ትገፋለች፥ ግፈኞችም ይናጠቋታል።

አ.መ.ት የማቴዎስ ወንጌል 11:12

> 12ከመጥምቁ ዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ መንግሥተ ሰማይ በብዙ ትገፋለች፤ የሚያገኟትም ብርቱዎች ናቸው፤

ህዝብ ሁሉ ሲመኝ ነበረውን እኛ አገኘነው ማለት ነው።

ስለዚህ መሲሁ ክርስቶስ መንግስቱን ለመመስረት ወደ ምድር ሲመጣ የ መሲሁ ይዞት የመጣው መንግስት የእኛ ይሆናል ማለት ነው። ስለዚህ የተሰሎንቄው ሀሳብ የተዘጋጀልንን መንግስት የእራሳችን እናደርጋለን። ክርስቶስ መንግስቱን ለመመስረት ወደ ምድር ሲመጣ የ መሲሁ ይዞት የመጣው መንግስት የእኛ ይሆናል ማለት ነው። እንጂ ወደ እላይ እንበራለን ማለት አይደለም።

# በዲስፔንሴሽናሎች አመለካከት በRUPTURE ጊዜ ምን ይሆናል?

ይህ የሰባቱ አመት መከራ የቤተክርስቲያንን ንጥቀት ተከትሎ በምድር ላይ የሚሆን የጭንቅ ጊዜ። በምድር ሰባቱ አመት ታላቁ መከራ ይሆናል፣ በሰማይ ደግሞ ሽልማታችንን እንቀበላለን ይላሉ።

አስቀድመን ሰባቱ አመት ታላቁን መከራ እንመልከት።

ይህ የሰባቱ አመት መከራ በሁለት ይከፍሉታል፦ የመጀመሪያው 3 አመት ተኩል የምጥ ጣር መጀመሪያ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ታላቁ መከራ በመባል ይታወቃል።

ይህንን ለማስረዳት ሁለት የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ይጠቀማሉ።

ትንቢተ ዳንኤል 12:1

> 1 “በዚያን ዘመን ስለ ሕዝብህ የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል። መንግሥታት ከተመሠረቱበት ጊዜ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ ታይቶ የማይታወቅ <u>ታላቅ የመከራ ጊዜ</u> ይሆናል።



GFX By: AD Graphics | +251916698510

### የማቴዎስ ወንጌል 24:21

> [21] በዚያን ጊዜ፣ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ሆኖ የማያውቅ፣ ከዚያም በኋላ የሚስተካከለው የሌለ፣ <u>ታላቅ መከራ</u> ይሆናል።

የታላቅ መከራ ሀሳብ መነሻ ጥቅሱ ይሄ ነው። ይህ Text Dispensationalኦች ስለሚያወሩት በ rupture ጊዜ ስለሚሆነው ታላቅ መከራ አይደለም። ይህንን ክፍል ማቴዎስ 24ትን ስናብራራው የምንመለከተው ይሆናል። ነገርግን በተቃራኒው በታላቅ መከራ ጊዜ ቤተክርስቲያን እንደምትኖር የመፅሐፍ ቅዱስ ይነግረናል።

### የዮሐንስ ራእይ 7:9-14

> [9] ከዚህም በኋላ አየሁ፤ እነሆ፤ በዙፋኑና በበጉ ፊት
> ማንም ሊቈጥራቸው የማይችል ከሕዝብ፣ ከነገድ፣ ከወገን፣
> ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሕዝብ ቆመው ነበር፤ እነርሱም
> ነጭ ልብስ ለብሰው፣ የዘንባባ ዝንጣፊ በእጃቸው ይዘው
> ነበር። [10] በታላቅ ድምፅም እንዲህ ብለው ጮኹ፤ "ማዳን
> በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው፣ የአምላካችንና የበጉ ነው።" [11]
> መላእክቱም ሁሉ በዙፋኑና በሽማግሌዎቹ፣ በአራቱም ሕያዋን
> ፍጡራን ዙሪያ ቆመው ነበር፤ በዙፋኑ ፊት በግንባራቸው
> ተደፍተው ለእግዚአብሔር ሰገዱ፤ [12] እንዲህም ይሉ ነበር፤
> "አሜን፤ ውዳሴና ክብር፣ ጥበብ፣ ምስጋናና፣ ሞገስ፣ ኀይልና
> ብርታትም፣ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ለአምላካችን
> ይሁን፤ አሜን።" [13] ከዚያም ከሽማግሌዎቹ አንዱ፣ "እነዚህ
> ነጭ ልብስ የለበሱት እነማን ናቸው? ከወዴትስ መጡ?"
> አለኝ። [14] እኔም፣ "ጌታ ሆይ፤ አንተ ታውቃለህ" አልሁት።
> እርሱም እንዲህ አለኝ፤ "እነዚህ **<u>ከታላቅ መከራ የመጡ</u>**
> **<u>ናቸው፤</u>** ልብሳቸውንም በበጉ ደም ዐጥበው አንጽተዋል።

በእዚህ ክፍል እንደምንመለከተው በግልጽ **<u>ከሕዝብ፣ ከነገድ፣ ከወገን፣ ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሕዝብ ቆመው ነበር</u>** ወይንም ቤተክርስቲያን በታላቁ መከራ ጊዜ ታልፋለች።

እዚህ ጋር Classical Dispensational እንደማሉት በዮሐንስ ራዕይ ላይ ቤተክርስቲያን ከምዕራፍ 4 ቀደም ብሎ ባለው ተነጥቃለች ይላሉ። ራዕይ 1–3 የChurch Age ነው። ሰባቱ አብያተክርስቲያናት የሚወክሉት የChurch ageን ነው ይላሉ።

ቤተክርስቲያን የተነጠቀችው ምዕራፍ 4:1 ላይ ነው

### ራእይ 4:1 (አዲሱ መት)

> "ከዚህ በኋላ እነሆ በሰማይ የተከፈተ በር አየሁ፤ ቀደም ሲል እንደ መለከት ሲናገረኝ የሰማሁት ድምፅ፦ "ወደዚህ ና፤ ከዚህም በኋላ ሊሆን የሚገባውን ነገር አሳይሃለሁ" አለ"

እዚህ ጋር ቤተክርስቲያን እንደተነጠቀች እንመለከትም ስንላቸው ፦ የሐንስን ቤተክርስቲያንን ይወክላል ይላሉ። ይህ ክፍል ስለ የሐንስ ብቻ እንጂ ስለቤተክርስቲያን እያወራ አይደለም።

የራዕይ መፅሐፍ ስለChronological Order እያወራ አይደለም(Cyclical ነው)

### 2ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1:7-10

> [7] መከራን ለተቀበላችሁት ለእናንተም ሆነ ለእኛ ደግሞ ዕረፍት
> ይሰጠናል። ይህም የሚሆነው ጌታ ኢየሱስ በሚንበለበል
> እሳት ከኀያላን መላእክት ጋር ከሰማይ በሚገለጥበት
> ጊዜ ነው። [8] በዚያ ጊዜ እግዚአብሔርን የማያውቁትንና
> ለጌታችንም ለኢየሱስ ወንጌል የማይታዘዙትን ይበቀላል።
> [9] እነርሱም ከጌታ ፊትና ከኀይሉ ክብር ተወግደው በዘላለም
> ጥፋት ይቀጣሉ፤ [10] የሚቀጡትም በቅዱሳኑ ዘንድ ሊከብርና
> በሚያምኑበትም ሁሉ ሊገረም በሚመጣበት በዚያን
> ቀን ይሆናል፤ እናንተም ከሚያምኑት መካከል ናችሁ፤



GFX By: AD Graphics | +251916698510

ምስክርነታችንን ተቀብላችኋልና፡፡

ጌታ ከሰማይ መላዕክት ጋር በሚገለጥበት ጊዜ ሁለት ነገር ይሆናል፡፡
**1ኛ|** ለፍርድ እና ለበቀል፡፡ **2ኛ|** በሚከራ የሚያልፉትን አማኞች ከመከራ ለማሳረፍ፡፡

2ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2:1-3

> 1 ወንድሞች ሆይ፤ ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና ወደ እርሱም ስለ መሰብሰባችን ይህን እንለምናችኋለን፤ 2 በመንፈስ ወይም በቃል ወይም ከእኛ እንደ ተላከ መልእክት የጌታ ቀን ደርሷል ብላችሁ ፈጥናችሁ ከአእምሮአችሁ አትናወጡ፤ አትደንግጡም፡፡ 3 ማንም ሰው በምንም መንገድ አያታልላችሁ፤ አስቀድሞ ዐመፅ ሳይነሣ፣ ለጥፋት የተመደበውም የዐመፅ ሰው ሳይገለጥ ያ ቀን አይመጣምና፡፡

ከክርስቶስ መምጣት በፊት የአመፅ ሰው ይገለጣል፡፡ መከራ ለማምጣት፡፡

## አክሊል

አክሊል ማለት በግሪክኛ እስጢፋኖስ ማለት ነው፡፡ ትርጉሙም የአበባ ጉንጉን ማለት ነው፡፡ Dispensationalኦች አክሊልን የሚረዱበትን መንገድ...አክሊል የዘለአለም ህይወትን ከማግኘት ጋር የሚያያዝ አይደለም፡፡ ነገር ግን ሰው ከዳነ በኋላ በታማኝነት በማገልገላቸው የሚሰጡ ሽልማቶች ናቸው ብለው ያምናሉ፡፡ የሽልማት ደረጃዎችን አንዱ ከአንዱ ይበላለጣል ብለው ያምናሉ፡፡ ይህንን ሽልማት የሚቀበሉት በክርስቶስ የፍርድ ወንበር በ(BEMA) እንጂ በነጩ ዙፋን ፍርድ አይደለም ይላሉ፡፡ የነጩ ዙፋን ፍርድ ላይ አማኞች አይቀርቡም፡፡ Dispensationalኦች አምስት አይነት ፍርዶች አሉ ይላሉ፡፡ ይህንን የመጨረሻውን ፍርድ ስንመለከት የምናየው ይሆናል፡፡ "bēma" የግሪክ ቃል ሲሆን ፡ ትርጉሙም ልዩ ፍርድ ቤት ማለት ነው፡፡ በጥንቷ ግሪክ ውስጥ ዳኞች በአትሌቲክስ ጨዋታዎች ውስጥ ሽልማቶችን የሚቀበሉበት ቦታ ነው፡፡ ጳውሎስ ይህንን ቃል ሲጠቀም የተጠቀመው አማኞችን በተመለከተ ብቻ ነው፡፡ ይህ ስለ መዳን ሳይሆን ስለ ሽልማት ነው ይላሉ፡፡

## አምስቱ የአክሊል አይነቶች፦

**1ኛ| የህይወት አክሊል(The Crown of Life)፦** ይህ አክሊል በፈተና ለመፀና እና በስደት ውስጥ ታማኝ ሆኖ ለሚቆይ ቃል ተገብቷል፡፡
የያዕቆብ መልእክት 1:12

> 12 በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ምክንያቱም ፈተናን ሲቋቋም እግዚአብሔር ለሚወድዱት የሰጠውን ተስፋ፣ የሕይወትን አክሊል ያገኛል፡፡

የዮሐንስ ራእይ 2:10

> 10 ሊደርስብህ ያለውን መከራ አትፍራ፡፡ እነሆ፤ ዲያብሎስ ሊፈትናችሁ አንዳንዶቻችሁን ወደ እስር ቤት ይጥላል፤ ዐሥር ቀንም መከራ ትቀበላላችሁ፡፡ እስከ ሞት ድረስ ታማኝ ሁን፤እኔም የሕይወትን አክሊል እሰጥሃለሁ፡፡

**2ኛ| የፅድቅ አክሊል(The Crown of Righteousness)፦** ይህ አክሊል የሚሰጠው የክርስቶስን ዳግም ምፅአት ለሚናፍቅ እና ዳግም ምፅአቱን በመጠባበቅ በፅድቅ ለሚኖር ሰው የሚሰጥ ሽልማት ነው፡፡

2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 4:8

> 8 ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፤ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ በዚያ ቀን ለእኔ ይሰጠኛል፤ ደግሞም ለእኔ ብቻ ሳይሆን፣ የእርሱን መገለጥ ለናፈቁ ሁሉ ነው፡፡

**3ኛ| የክብር አክሊል(The Crown of Glory)፦** የእግዚአብሔርን ህዝብ በጥንቃቄ እና በትጋት ለሚጠብቁ ሽማግሌዎች ወይም ለቤተክርስቲያን መሪዎች የሚሰጥ ሽልማት ነው፡፡ Faithful pastors, elders, and spiritual leaders

1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 5:4

> 4 የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ፡፡



GFX By: AD Graphics | +251916698510

**4ኛ| የደስታ አክሊል/የነፍስ አሸናፊ አክሊል ተብሎ ይጠራል The Crown of Rejoicing (Soul Winner's Crown)፦** ያልዳኑ ነፍሳትን ወደ ክርስቶስ ለሚጠሩ ይሰጣል፡፡

1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2:19-20

> 19 ተስፋችን ወይስ ደስታችን ወይስ የትምክህታችን አክሊል ማን ነው? በጌታችን በኢየሱስ ፊት በመምጣቱ እናንተ አይደላችሁምን? 20 እናንተ ክብራችን ደስታችንም ናችሁና፡፡

**5ኛ| የማይጠፋው አክሊል(The Imperishable Crown (Incorruptible Crown)፦** እራሳቸውን ተግሳጽ ለሚያደርጉ እና እራሳቸውን የተስተካከለ ህይወት ለሚመሩ ነው፡፡

1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 9:25

> 25 ለውድድር የሚዘጋጅ ማንኛውም ሰው በሁሉም ነገር ራሱን ይገዛል፤ እነርሱ ዐላፊ ጠፊ የሆነውን አክሊል ለማግኘት ይደክማሉ፤ እኛ ግን ለዘላለም የማይጠፋውን አክሊል ለማግኘት እንደክማለን፡፡

በህይወት አክሊል እና በዘለአለም ህይወት መካከል÷በፅድቅ አክሊሉ እና በመፅደቃችን መካከል÷ በክብር አክሊል እና በ Glorification መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? በማይጠፋ አክሊል እና በማይጠፋ ህይወት መካከል ምንድነው ልዩነቱ? ደግሞስ ሌሎች አክሊሎች የሚጠፉ ናቸው? በክርስቶስ በሚገኘው ሙሉ ደስታ እና በደስታ አክሊልስ?

## ስለ ሽልማት ሐዋሪያቱ ምን ያስቡ ነበር?

1ኛ| የሰዎች መዳንን እንደ አክሊል ይመለከቱታል፡፡

1ኛ ተሰሎንቄ 2፡19 (አዲሱ መ.ት)

> "ጌታችን ኢየሱስ ሲመጣ በእርሱ ፊት ተስፋችን ወይም ደስታችን ወይም አክሊላችን ማን ነው? እናንተ አይደላችሁምን?"

ፊልጵስዩስ 4፡1 (አዲሱ መ.ት)

> "ስለዚህ የምወዳችሁና የምናፍቃችሁ፣ ወንድሞቼ ደስታዬና አክሊሌ የሆናችሁ፣ እንዲሁም ወዳጆች ሆይ፤ በዚህ ሁኔታ በጌታ ጸንታችሁ ቁሙ፡፡"

2ኛ| በወንጌል የሚገኘው Satisfaction/እርካታ

1ኛ ቆሮንቶስ 9 (አዲሱ መ.ት)

> 18 ታዲያ ሽልማቴ ምንድን ነው? ሽልማቴማ ወንጌልን ስሰብክ በመብቴ ሳልጠቀም ወንጌልን ያለ ክፍያ መስበክ ነው፡፡ ……… 24 በሩጫ ውድድር የሚሮጡ ብዙዎች እንደሆኑ፣ ሽልማቱን የሚቀበለው ግን አንዱ ብቻ እንደሆነ አታውቁምን? ስለዚህ ሽልማቱን እንደሚቀበል ሰው ሩጡ፡፡

3ኛ| ድነትን በሙላት ማግኘታቸውን እንደ አክሊል ይቆጥሩታል፡፡

2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡8 (አዲሱ መ.ት)

> "ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፤ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ በዚያ ቀን ለእኔ ይሰጠኛል፤ ደግሞም ለእኔ ብቻ ሳይሆን፣ የእርሱን መገለጥ ለናፈቁ ሁሉ ነው፡፡"

ይህ ሽልማት ለሁሉም አማኞች ነው፡፡ **<u>የእርሱን መገለጥ ለናፈቁ ሁሉ ነው</u>**፡፡ የክርስቶስ የሆኑት ድነትን በሙላት ይቀበላሉ፡፡ በምድር ለምንሰራው መልካም ስራዎች በምድር መልካም ነገር ያስገኙልናል እንጂ በሰማይ አይደለም፡፡

የማርቆስ ወንጌል 10:29-30

> 29 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለ፤ "እውነት እላችኋለሁ፤ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ሲል ቤቱን ወይም ወንድሞቹን ወይም እኅቶቹን ወይም እናቱን ወይም አባቱን ወይም ልጆቹን ወይም ዕርሻውን የተወ ሁሉ፣ 30 አሁን በዚህ ዘመን ከስደት ጋር ቤቶችን፣ ወንድሞችን፣ እኅቶችን፣ እናቶችን፣ ልጆችንና ዕርሻን መቶ ዕጥፍ የማይቀበል፣ በሚመጣውም ዓለም የዘላለም ሕይወት የማይወርስ የለም፡፡

በወንጌል ምክንያት የክርስቶስ ሆኖ ከቤተሰብ የተገለለ ሰው በምድር እግዚአብሔር ይክሰዋል። በሰማይ የሚጠብቀው ደግሞ የዘለአለም ህይወት አለ። በሰማይ ከዘለዓለም ህይወት ውጪ ሌላ የሚጠብቀን ነገር ቢኖር ይነገርነን ነበር።

በጣም የሚገርመው ዲስፔንሴሽናሎች በምድር ለምንሰራው መጥፎ ነገር በምድር እንጂ በሰማይ አንቀበልም ይላሉ። ከድነት ውጪ የምንጠብቀው ሌላ ምንም ነገር እንደሌለ 4 ምክንያቶችን እንመልከት፦

1. Crowns symbolic እንጂ literal አይደለም። የVictory, የመፅናት፣ Salvation እና Eternal life metaphors ነው።

2.Rewards በሰማይ Inequalityን ይፈጥራል። በሰማይ እኩል እና ፍፁም ደስታ ነው ያለው እንጂ መበላለጥ የለም።

3.ሁላችንም በጌታ ፀጋ ከሰራን አንዱ ከአንዱ በእራሱ ችሎታ እንደሰራ ነገር የተለየ ሽልማት ሊሰጠው አይገባም።

1ኛ ቆሮንቶስ 4፥7 (አዲሱ መ.ት)

"ለመሆኑ፣ አንተን ከሌላው እንድትበልጥ ያደረገህ ማን ነው? ያልተቀበልኸው የራስህ የሆነ ነገር ምን አለ? ከተቀበልህ ታዲያ፣ እንዳልተቀበልህ ለምን ትመካለህ?"

1ኛ ጢሞቴዎስ 1፥12 (አዲሱ መ.ት)

"በአገልግሎቱ በመሾም ታማኝ አድርጎ የቈጠረኝን፣ ብርታት የሰጠኝን ጌታችንን ክርስቶስ ኢየሱስን አመሰግናለሁ።"

4. በሰማይ ቀጥተኛ በሆነ መንቀዱ አክሊል በእራሳችን ላይ እንደፋለን ብለን ብናስብ እንኳን ፤ የምንድነው ጥቅሙ? በሰማይ focus የሚደረገው ክርስቶስ ላይ እንጂ የእኛ reward ላይ አይደለም።

ራእይ 4፥10 (አዲሱ መ.ት)

"ሃያ አራት ሽማግሌዎች በዙፋኑ ላይ በተቀመጠው ፊት ተደፍተው፣ ከዘላለም እስከ ዘላለም ሕያው ሆኖ ለሚኖረው ይሰግዱ ነበር፤ አክሊላቸውንም በዙፋኑ ፊት አስቀምጠው እንዲህ ይላሉ፤"

## PRETERIST፣ HISTORICIST፣ IDEALIST እና FUTURIST

የ**Preterist**ን view አስቀድመን ተመልክተናል። ከእዚህ በኋላ የሚፈፀም ምንም አይነት ትንቢት የለም ብለው የሚያምኑ ናቸው።

### Historicist:

እነዚህ ለምሳሌ ፦ ፍላድልፍያ የምትባለው ቤተክርስቲያን የተነገረው ትንቢት ከእዛ በኋላ ባሉት ዘመናት በታሪክ ውስጥ ከየትኛው ዘመን ጋር እንደሚገናኝ እና እንዴት እንደተፈፀመ የሚያብራሩ ናቸው። ትንቢቶቹ በእየዘመኑ መፈፀሙን የሚያስረዱ ናቸው። ለምሳሌ፦ አውሬው=የሮማ ካቶሊክ ፓፓ ነው ምናምን እያሉ የሚተረጉሙ ናቸው። በሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የተነገሩ ነገሮችን ፦ ይሄው ይህ የሮም ውድቀት ነው፣ ይህ የእስልምና መነሳትነው፣ ይህ የፕሮቴስታንት ተሃድሶ እንቅስቃሴ ነው እያሉ የሚያብራሩ ናቸው።

### Idealist:

እነዚህ ደሞ፦ የራዕይ መፅሀፍ መጥፎ እና ጥሩ fight ሲያደርጉ ነው እንጂ የሚያሳየው፤ ስለሚፈፀም የሆነ ትንቢት አይደለም የሚያሳየው ይላሉ። ሁሌም ክፉ እንደሚሸነፍ፣ መልካም ደግሞ እንደሚያሸንፉ ለማሳየት የተጠቀመበት ምሳሌ ነው እንጂ Real አይደለም የሚሉ ናቸው።

### Futurist:

በራዕይ የምንመለከታቸው አብዛኛዎቹ መገለጦች ፤ በመጨረሻው ዘመን የሚከናወኑትን ክስተቶች እንደሆኑ ያስባሉ። ለምሳሌ፦ መነጠቅ ፣ ታላቁ መከራ፣ የሺኛው መንግስት። ወዘተረፈ። የእነዚህን ምልከታ ጥንካሬ እና



GFX By: AD Graphics | +251916698510

ጉድለት ወደ ጥናቱ ዘልቀን ስንገባ እንመለከታለን፡፡

## እስራኤል ሁሉ ይድናል

ይህ ምልከታ ለDispensationalኦች ዋናውን ስፍራ የሚይዝ በመሆኑ ማብራሪያቱ እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ ምክንያቱም የDispensationalኦች አብዛኛው ስህተት ከእዚህ ነው የሚጀምረው፡፡ እያንዳንዱ እስራኤላውያን ይድናሉ የሚለውን አስተሳሰብ ከሮሜ 11 ነው የወሰዱት፡፡

– ሮሜ 11 (አዲሱ መ.ት)

26 ስለዚህ እስራኤል ሁሉ ይድናሉ፤ እንዲህ ተብሎ እንደ
ተጻፈ፤ “አዳኝ ከጽዮን ይወጣል፤ ከያዕቆብም ክፋትን
ያስወግዳል፡፡ 27 ኀጢአታቸውንም ሳስወግድ፣ ከእነርሱ ጋር
የምገባው ኪዳኔ ይህ ነው፡፡”

ከእዚህ ክፍል ተነስተው Each and every Individual jew ይድናል ብለው ያምናሉ፡፡ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የገባውን ኪዳን ስላላቋረጠ ለእስራኤል የተሰጠው ተስፋ በእስራኤል ይፈፀማል ብለው ያምናሉ፡፡ ይህንንም የሚያብራሩት፦ ከሰባቱ አመት መከራ በፊት ኢየሱስ በስውር ይመጣል፥ ቅዱሳንን ከሞት ይቀሰቅሳል፣ ከእዚያ ቤተክርስቲያን ትነጠቃለች፡፡ በሰባት አመት በሰማይ የበጉ እና የቤተክርስቲያን ሰርግ ይሆናል፣ በምድር ላይ ደግሞ አውሬው ይነግሳል፥ ከእስራኤልም ጋር ቤተመቅደስ ለመስራት ቃልኪዳን ይገባል፡፡

ከእዚያም ለሶስት አመት ተኩል ሰላም ይሆናል፤ በቤተመቅሱ ጣኦት ያቆማል፣ በምድር ላይ ታላቅ መከራ ይሆናል፣ እስራኤልን አጥብቆ ያስጨንቃል፡፡ የአርማ ጌዲዮን ጦርነት በእስራኤል እና በተቀረው አለም መካከል ያደርጋል፡፡ በእዚህ የጭንቅ ጊዜ እስራኤልን ለመታደግ ኢየሱስ በመላዕክት ታጅቦ ከሰማይ ይገለጣል፡፡ ከቤተክርስቲያን ጋር ከሰማይ ይወርዳል፣ የእስራኤልን ጠላቶች ይመታል፣ በምድርም የአንድ ሺ መንግስት ይመሰርታል፡፡

ሰይጣን የእስራኤልን ህዝብ ለማጥፋት የሚጥርበት ምክንያት መሲሁ መጥቶ የእስራኤል ህዝብ ላይ ስለሚነግስ ነው ይላሉ፡፡ ስለዚህ ሰይጣን ምን ያስባል?፦ በመጀመሪያው ምፅአቱ ተሸውጃለሁ፣ በዳግም ምፅአቱ ደግሞ የሚነግሰው እስራኤል ላይ ከሆነ እኔን መከራ ያበላኛል፡፡ ስለዚህ እስራልን ባጠፋት ማን ላይ መጥቶ ይነግሳል፡፡ ስለዚህ ሳይመጣ በፊት የሚነግስበትን ህዝብ አጠፋለሁ ይላል ይላሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ሰይጣንን እንኳን የዲስፔንሴሽናል Theologyን እንዲያስብ አድርገዋል፡፡ አሁን ላይ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ምንም አይነት ውል የለውም፡፡

ማቴዎስ 21 (አዲሱ መ.ት)

33 “ሌላም ምሳሌ ስሙ፤ አንድ የወይን ዕርሻ ባለቤት
ነበረ፤ በዕርሻው ዙሪያ አጥር አጠረ፤ ለወይኑ መጭመቂያ
ጉድጓድ ቈፈረ፤ ለጥበቃ የሚሆን ማማ ሠራ፤ ከዚያም
ዕርሻውን ለገበሬዎች አከራይቶ ወደ ሌላ አገር ሄደ፡፡ 34
የመከር ወራት ሲደርስ፣ ፍሬውን ለመቀበል አገልጋዮቹን
ወደ ገበሬዎቹ ላካቸው፡፡ 35 “ገበሬዎቹም አገልጋዮቹን
ይዘው አንዱን ደበደቡት፤ ሌላውን ገደሉት፤ ሌላውን ደግሞ
በድንጋይ ወገሩት፡፡ 36 እርሱም ከፊተኞቹ የሚበልጡ
ሌሎች አገልጋዮቹን ላከ፤ ገበሬዎቹም ተመሳሳይ ድርጊት
ፈጸሙባቸው፡፡ 37 በመጨረሻም፣ ‘ልጄን ያከብሩታል’ በማለት
ልጁን ላከ፡፡ 38 “ነገር ግን ገበሬዎቹ ልጁን ባዩት ጊዜ፣ ‘ይህማ
ወራሹ ነው፤ ኑ፣ እንግደለውና ርስቱን እንውረስ’ ተባባሉ፡፡
39 ይዘውም ከወይኑ ዕርሻ ውጭ አውጥተው ገደሉት፡፡ 40
“ታዲያ የወይኑ ዕርሻ ባለቤት ሲመጣ እነዚያን ገበሬዎች ምን
የሚያደርጋቸው ይመስላችኋል?” 41 እነርሱም፣ “እነዚያን
ክፉዎች በአሰቃቂ ሁኔታ ገድሎ ከወይኑ ዕርሻ ተገቢውን
ፍሬ በወቅቱ ለሚያስረክቡት ለሌሎች ገበሬዎች ያከራያል”
አሉት፡፡ 42 ኢየሱስም እንዲህ ተብሎ በቅዱሳት መጻሕፍት
የተጻፈውን አላነበባችሁምን? አላቸው፤ “ ‘ግንበኞች


GFX By: AD Graphics | +251916698510

> የናቀት ድንጋይ፣ የማእዘን ራስ ሆነ፤ እግዚአብሔር ይህን
> አድርጎአል፤ ሥራውም ለዐይናችን ድንቅ ነው።’ 43 “ስለዚህ
> እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ከእናንተ ተወስዳ
> ፍሬዋን ለሚያፈራ ሕዝብ ትሰጣለች፤

የቃል ኪዳን ተስፋዎች ሁሉ ከማያምኑ እስራኤላውያን ወደ ቤተክርስቲያን መለወጡን በቀጥታ እየጠቆመን ነው። ይህ ነው Replacement theology. በአጭሩ ቤተክርስቲያን እውነተኛ እስራኤል ናት። ወይንም ቤተክርስቲያን “አዲሱ እስራኤል” ናት።

### ኤፌሶን 2 (አዲሱ መ.ት)

> 14 ሁለቱን አንድ ያደረገ፣ የሚለያየውንም የጥል ግድግዳ
> ያፈረሰ ሰላማችን እርሱ ራሱ ነውና፤ 15 ሕግንም፣ ከትእዛዛቱና
> ከሥርዐቱ ጋር በሥጋው ሻረ። ዐላማውም ከሁለቱ አንድን
> አዲስ ሰው በራሱ ፈጥሮ ሰላምን ለማድረግ ነው። 16
> ጥልን በገደለበት በመስቀሉም ሁለቱን በዚህ በአንድ
> አካል ከእግዚአብሔርጋር አስታረቀ። 17 መጥቶም ርቃችሁ
> ለነበራችሁት ለእናንተ፣ ቀርበው ለነበሩትም ለእነርሱ ሰላምን
> ሰበከ፤ 18 ሁላችንም በእርሱ አማካይነት በአንዱ መንፈስ
> ወደ አብ መቅረብ እንችላለንና።

### ገላትያ 3 28-29

> “በአይሁድና በግሪክ፣ በባሪያና በነጻ ሰው፣ በወንድና በሴት መካከል ልዩነት የለም፤ ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ናችሁ።”የክርስቶስ ከሆናችሁ፣ እናንተ የአብርሃም ዘር ናችሁ፤ እንደ ተስፋውም ቃል ወራሾች ናችሁ።”

የዘር ልዩነት ፣ የደረጃ ልዩነት ፣ የፆታ ልየነት። እነዚህ ነገሮች ላይ ከመፅደቅ አንፃር ምንም ዋጋ የላቸውም። የአብርሃም ዘር መሆን የሚቻለው በክርስቶስ በመሆን ነው። ስለዚህ ምን እያለ ነው በክርስቶስ ያልሆነ ከአብረሃም በስጋ የተወለደ ሁሉ የአብርሃም ዘር አይደለም እያለ ነው። ይህንን ለሚሰማ አንድ ordinary Jew እራስምታት ይይዘዋል። ክርስቶስ ከመጣ በኋላ የእግዚአብሔር ህዝብ ተብለው የሚጠሩት በዘር እና በብሄር ሳይሆን በክርስቶስ በማመን ነው።

## ሮሜ 11:26

የእዚህን የሮሜ 11:26ን ለመረዳት ሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎችን እንጠይቅ።

1ኛ, እስራኤል ሁሉ ይድናል ማለት ምን ማለት ነው ምን ማለትስ አይደለም?
2ኛ, እንዴት እና ከምንድነው የሚድኑት?
3ኛ, እስራኤል ሁሉ ይድናል ብሎ ለወደፊት በተስፋ የነገረን መቼ ነው ይህ ትንቢት የሚፈፀመው?

**የመጀመሪያውን አስቀድመን እንመልከት፦** እስራኤል ሁሉ ይድናል ማለት ምን ማለት ነው ምን ማለትስ አይደለም?

እስራኤል ሁሉ ይድናል ማለት እያንዳንዱ እስራኤላውያን ይድናሉ ማለት አይደለም። ታዲያ እስራኤል ሁሉ ይድናል ማለት ምን ማለት ነው? እስራኤል ማለት በስጋ አይሁድ የሆኑ ሁሉ ማለት ሳይሆን ከመካከላቸው በፀጋ የመረጣቸው ቅሬታዎች ሁሉም ይድናሉ ማለት ነው።

ታዲያ ሮሜ 11:26 ላይ እስራኤል ሁሉ ይድናል ሲል ምን እያለ ነው? ይህንን ለመረዳት ከምዕራፍ 9 እንጀምር።

### ሮሜ 9 (አዲሱ መ.ት)

> 6 ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል ተሽሮአል ማለት አይደለም፤
> ከእስራኤል የተወለደ ሁሉ እስራኤላዊ አይደለምና። 7
> ከአብርሃም ዘርም ስለሆኑ፣ ሁሉም ልጆቹ አይደሉም፤
> ይልቁንስ፣ “ትውልድህ በይሥሐቅ በኩል ይጠራልሃል”
> እንደ ተባለው ነው። 8 ይህም ማለት የእግዚአብሔር ልጆች
> የተባሉት የሥጋ ልጆች አይደሉም፤ ነገር ግን የአብርሃም
> ልጆች የተባሉት የተስፋው ልጆች ናቸው።



GFX By: AD Graphics | +251916698510

አብርሃም ሁለት ልጆች አሉት፡፡ እስማኤል እና ይስሃቅ፡፡ እስማኤል የተወለደው ከአጋር ሲሆን፣ ይስሃቅ የተወለደው ከሳራ ነው፡፡ እስማኤል እንደ ስጋ ፈቃድ ነው የተወለደው፣ ይስሃቅ ደግሞ እንደ መንፈስ ፈቃድ ነው(የተስፋ ቃል ልጅ) የተወለደው፡፡ አብርሃም ሶስት ሚስቶች አሉት፡፡ ሳራ፣ አጋር አና ኬጡራ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ከሶስቱም ልጆችን ወልዷል፡፡ ከሶስቱ ልጆች ቢኖሩትም እግዚአብሔር ተሰፋውን የሰጠው ለይስሃቅ ዘር እንጂ ለሌሎቹ አይደለም፡፡ ከሶስቱ የታራን ልጆች እግዚአብሔር አብረሃምን መረጠ፣ ከሶስቱ የአብርሃ ሚሰቶች ሳራን መረጠ፣ ከስምንቱ የአብርሃም ልጆች ደግሞ ይስሃቅን መረጠ፡፡ እግዚአብሔር ለይስሃቅ ተስፋን ሰጠው፡፡ የአብርሃም ልጅ መሆን የእግዚአብሔር ልጅነትን መብት አያሰጥም፡፡ የእግዚአብሔር ልጅነት መብት የሚያሰጠው በእግዚአብሔር መመረጥ ነው፡፡ ርብቃ ከያዕቆብ 2 ልጆችን ወልዳለች፡፡ ያዕቆብ እና ኤሳው፡፡ እግዚአብሔር ያዕቆብን ለቃልኪዳን ይመርጠዋል፣ ይስሃቅን ግን ይተወዋል፡፡ ያዕቆብን ወደዱኩት ኤሳውን ጠላሁት ነው የሚለው፡፡

ቁጥር 8 ላይ **የሥጋ ልጆች** እና **የእግዚአብሔር ልጆች** ብሎ ይከፋፍላል፡፡ የስጋ ልጆች የሚለው ከአብረሃም በስጋ የተወለዱትን ሲሆን የእግዚአብሔር ልጆች የሚለው ደግሞ እንደ ተስፋ ቃል የተወለዱት ናቸው፡፡ ስለዚህ ከአብረሃም በስጋ መወለድ የእግዚአብሔር ልጅ አያደርግም፡፡ ይህንን አመለካከታቸውን አስቀድሞም በምዕራፍ 2 ላይ ለማረም ሞክሮ ነበር፡፡

**ሮሜ 2 (አዲሱ መ.ት)**

28 አንድ ሰው ለይምሰል በውጫዊው ብቻ ይሁዲ ልሁን
ቢል ይሁዲ አይሆንም፤ እውነትኛ ግዝረትም ውጫዊና
ሥጋዊ ሥርዐት አይደለም፡፡ 29 ዳሩ ግን አንድ ሰው ይሁዲ
የሚሆነው በውስጣዊ ማንነቱ ይሁዲ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡
ግዝረትም ግዝረት የሚሆነው በተጻፈው ሕግ ሳይሆን፣
በመንፈስ የልብ ግዝረት ሲኖር ነው፡፡ እንዲህ ያለው ሰው
ምስጋናው ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው፡፡

ስለዚህ በስጋው የተገረዘ ሁሉ ልቡ የተገረዘ አይደለም እያለ ነው፡፡

**ገላትያ 6፥16 (አዲሱ መ.ት)**

"ይህን ትእዛዝ በሚከተሉ ሁሉ፣ የእግዚአብሔር በሆነው እስራኤልም ላይ ሰላምና ምሕረት ይሁን፡፡"

ይህ በስጋ በሆነው እስራኤል እና የእግዚአብሔር በሆነ እስራኤል መካከል ያለውን ልዩነት የሚያመለክት፡፡ በእስራኤል ህዝብ መካካል የእግዚአብሔር የሆነ እስራኤል እና የእግዚአብሔር ያልሆነ እስራኤል አለ፡፡

**ሮሜ 11**

1 እንግዲህ እግዚአብሔር ሕዝቡን ተዋቸውን? ብዬ
እጠይቃለሁ፤ በፍጹም! እኔ ራሴ ከብንያም ነገድ፣ የአብርሃም
ዘር የሆንሁ እስራኤላዊ ነኝ፡፡ 2 እግዚአብሔር አስቀድሞ
ያወቃቸውን ሕዝብ አልጣላቸውም፡፡ ኤልያስ በእስራኤል
ላይ ክስ ወደ እግዚአብሔር እንዴት እንዳቀረበ፣ መጽሐፍ
ስለ እርሱ ምን እንደሚል አታውቁምን? 3 "ጌታ ሆይ፤
ነቢያትህን ገድለዋል፤ መሠዊያዎችህን አፍርሰዋል፤ እኔም
ብቻዬን ቀረሁ፤ ሊገድሉኝም ይፈልጋሉ፡፡" 4 እግዚአብሔር
የሰጠው መልስ ግን ምን ነበር? "ለበኣል ያልሰገዱትን ሰባት
ሺህ ሰዎች ለራሴ አስቀርቻለሁ፡፡" 5 በአሁኑ ጊዜም እንደዚሁ
በጸጋ የተመረጡ ትሩፋን አሉ፡፡

**ሮሜ 11፥7**

"እንግዲህ ምንድን ነው? እስራኤል አጥብቀው የፈለጉትን አላገኙትም፤ የተመረጡት ግን አገኙት፤ የቀሩትም ልባቸው ደነደነ፤"

እነዚህን ሁሉ ክፍል ይዘን በፍፁም በስጋ እስራኤላዊ የሆነ ሁሉ ይድናል ወደሚለው ድምዳሜ ልንደርስ አንችልም፡፡ <u>እዚህ ጋር ሁለት ጥያቄዎችን እንጠይቅ</u>፦


GFX By: AD Graphics | +251916698510

1ኛ, ሁሉም እስራኤላውያን የሚድኑ ከሆነ ምዕራፍ 2:9 ላይ የጳውሎስ ጭንቀት ለምን አስፈለገ? እንዲሁም ምዕራፍ 10:1 ላይ ምን አስለመነው?

ሮሜ 9፥2 (አዲሱ መ.ት)

"ታላቅ ሐዘንና የማያቋርጥ ጭንቀት በልቤ አለ።"

ሮሜ 10፥1 (አዲሱ መ.ት)

"ወንድሞች ሆይ፤ ስለ እስራኤላውያን የልቤ ምኞት፣ እግዚአብሔርንም የምለምነው እንዲድኑ ነው።"

2ኛ, እያንዳንዱ እስራኤል ይድናል እያለ ከሆነ ቀቅሬታዎቹ ይድናሉ ማለት ምን ማለት ነው?

ቅሬታ ማለት የብዙ ክፍል ትንሹ ማለት ነው። አንድ አራተኛው እንኳን የማይሆን ማለት ነው። HC ባያስቀርልን የሚለው የእርሻን ምሳሌን እየተጠቀመ ነው። ለምሳሌ ገብሬ፦ በመከር ጊዜ መከር ከሰበሰቡ በኋላ ከእህሉ በጣም ጥቂት የሆነውን ክፍል ለHC ያስቀራሉ። ይህ ለHC የሚያስቀሩት እህል በጣም ጥቂት ነው። ለምሳሌ መቶ ኩንታል እህል ቢሆን አንድ ኩንታል እህል ይሆናል።

2ኛ, እንዴት እና ከምንድነው የሚድኑት? ከምንድነው የሚድኑት?

ከፖለቲካዊ ነገር ሳይሆን የሚድኑት ከኃጢአት ነው የሚድኑት። የDispensationalኦችን አተረጓጎም ከተመለከትን ፓለቲካዊ ነው። በታላቁ መከራ ጊዜ የአመፅ ሰው እስራኤልን አጥብቆ ያስጨንቃል። የአርማ ጌዲዮን ጦርነት በእስራኤል እና በተቀረው አለም መካከል ያደርጋል። በእዚህ የጭንቅ ጊዜ እስራኤልን ለመታደግ ኢየሱስ በመላዕክት ታጅቦ ከሰማይ ይገለጣል። ከቤተክርስቲያን ጋር ከሰማይ ይወርዳል፣ የእስራኤልን ጠላቶች ይመታል፣ በምድርም የአንድ ሺ መንግስት ይመሰርታል ይላሉ። ነገር ግን የተመረጡት እስራኤላውያን ከ ዘለአለማዊ ፍርድ ነው የሚድኑት።

- <u>እንዴት ነው የሚድኑት</u>?

  ይህ ፅድቅ በማመን እንደሚገኝ ምዕራፍ 10 ላይ ይገልጻል። ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን የሚገኝ ፅድቅ ነው።

ሮሜ 10:12

12 በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ልዩነት የለም፤ አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና፤ የሚለምኑትንም አብዝቶ ይባርካል፤

ሮሜ 11፥23 (አዲሱ መ.ት)

"እነርሱም ባለማመናቸው ጸንተው ባይኖሩ፣ ተመልሰው ይገባሉ፤ እግዚአብሔር መልሶ ሊያስገባቸው ይችላልና።"

3ኛ, እስራኤል ሁሉ ይድናል ብሎ ለወደፊት በተስፋ የነገረን መቼ ነው ይህ ትንቢት የሚፈፀመው?

1ኛ, በዘመናት ሁሉ ያሉትን እስራኤላውያን አይወክልም።

2ኛ, እኛ የምንስበው አይነት Eschatological አይደለም።

ይህ ትንቢት በእዚያው ዘመን ተፈፅሟል። ማለትም በሮሜ የተነገረው ትንቢት በሐዋርያት ስራ ተፈፅሟል። የሮሜ መፅሐፍ 56–58 ዓ.ም ነው የተፃፈው ተብሎ ይታመናል። የሐዋርያት ስራ ደግሞ ከ62–64 ባለው እንደተፃፈ ይታመናል።

ሐዋርያት 21፥20 (አዲሱ መ.ት)

"እነርሱም ይህን ሲሰሙ፣ እግዚአብሔርን አመሰገኑ፤ ጳውሎስንም እንዲህ አሉት፤ "ወንድም ሆይ፤ በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ አይሁድ እንዳመኑ ተመልከት፤ ሁሉም ደግሞ ለሙሴ ሕግ የሚቀኑ ናቸው።"

ጳውሎስ እሱ ስላለበት ዘመን ስለሚፈፀም ነገር እያወራ እንደሆነ የምንረዳው ቁጥር 5 ነው።

ሮሜ 11፥5 (አዲሱ መ.ት)

"<u>በአሁኑ ጊዜም</u> እንደዚሁ በጸጋ የተመረጡ ትሩፋን አሉ።"

ጳውሎስ ከእርሱ ዘመን በኋላ ስለሚመጡት ጊዜያት እያሰበ አይደለም የፃፈው። የአህዛብ ሙላት እስኪሆን በእስራኤል ላይ ድናዳኔ የሚሆን ከሆነ ይሄ ሁሉ ሰው እንዴት ሊድን ይችላል?



GFX By: AD Graphics | +251916698510

ስለዚህ በእዚያን ዘመን በጳውሎስ ስብከት እግዚአብሔር የሚፈልገው የአህዛብ ቁጥር ሲሞላ እስራኤላውያን መዳን እንደጀመሩ የሚያመለክት መሆን አለበት። ኢየሱስ በሚመጣበት ጊዜ እስራኤል የሚባል ማህበረሰብ እንደሚድን አንድም የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍልየለም።

## ፱ "ሺ" ኛው ዘመነ መንግስት

መፅሐፍ ቅዱስ በሺኛው ዘመነ መንግስት ስለሚፈፀሙ ነገሮች እና ስለ ሺኛው መንግስት በዮሐንስ ራዕይ 20 ላይ ይነገርናል።

ራእይ 20 (አዲሱ መ.ት)

1 የጥልቁን መክፈቻና ትልቅ ሰንሰለት በእጁ የያዘ መልአክ
ከሰማይ ሲወርድ አየሁ። 2 እርሱም የጥንቱን እባብ፣
ዘንዶውን፣ ማለትም ዲያብሎስን ወይም ሰይጣንን ይዞ ሺህ
ዓመት አሰረው። 3 ሺሁ ዓመትም እስኪፈጸምም ድረስ
ከእንግዲህ ወዲህ ሕዝቦችን እንዳያስት ወደ ጥልቁ ጣለው፤
ዘጋውም፤ በእርሱም ላይ ማኅተም አደረገበት። ከዚያ በኋላ
ለጥቂት ጊዜ ሊፈታ ይገባዋል። 4 ቀጥሎም ዙፋኖችን
አየሁ፤ በዙፋኖቹም ላይ ለመፍረድ ሥልጣን የተሰጣቸው
ሰዎች ተቀምጠው ነበር፤ ደግሞም ስለ ኢየሱስ ምስክርና
ስለ እግዚአብሔር ቃል የተሰየፉትን ሰዎች ነፍሶች አየሁ።
እነርሱ ለአውሬው ወይም ለእርሱ ምስል አልሰገዱም፤
በግምባራቸው ወይም በእጃቸው ላይ የአውሬውን ምልክት
አልተቀበሉም፤ እነርሱም ከሞት ተነሥተው ከክርስቶስ
ጋር ሺህ ዓመት ነገሡ። 5 የቀሩት ሙታን ግን ሺሁ ዓመት
እስኪፈጸም ድረስ ከሞት አልተነሡም። ይህ የመጀመሪያው
ትንሣኤ ነው። 6 በመጀመሪያው ትንሣኤ ተካፋይ የሚሆኑ
ብፁዓንና ቅዱሳን ናቸው። ሁለተኛው ሞት በእነርሱ ላይ
ሥልጣን የለውም፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርና የክርስቶስ
ካህናት ይሆናሉ፤ ከእርሱም ጋር ሺህ ዓመት ይነግሣሉ።

ከሺኛው መንግስት ጋር በተያያዘ ሶስት ዋና ዋና ምልከታዎች አሉ።

1ኛ, Premillennialism ቅድመ ሺ አመት (ከሺው አመት መንግስት በፊት ክርስቶስ ቀድሞ ይመጣል።)

2ኛ, Postmillennialism. ድህረ ሺ አመት (ከሺው አመት መንግስት በኋላ ክርስቶስ ይመጣል።)

3ኛ, Amillennialism አልቦ ሺ አመት (የሺኛው መንግስት አመት አፈፃፀም በምድራዊ መንግስት ሳይሆን አሁን ባለው በክርስቶስ መንፈሳዊ መንግስት ነው።)

የእነዚህ አስተሳሰብ ሙግት እንደ እግዚአብሔር ቃል ለመሞገትእንሞክራለን።

PREMILLENNIALISM

# ቅድመ ሺ አመት ምልከታ

የአብርሃም ተስፋ በክርስቶስ የመጀመሪያው ምፅአቱ ተፈፅሟል። የዳዊት ተስፋ ግን ለወደፊት በ ሺኛው መንግስት በሁለተኛው ምፅአቱ የሚፈፀም ነው ብለው ይጠብቃሉ። በዳዊት ዙፋን ይቀመጣል የሚለውን ተስፋ ይጠብቃሉ።

ኢየሱስ ለወደፊት የሚሾም ንግስ ነው። ሺኛው መንግስት literal ነው ብለው የማያምኑ ናቸው። በጥሬውተቆጥሮ 1000 አመት ክርስቶስ በምድር ላይ ይነግሳል ብለው ያምናሉ። ኢየሱ በመጀመሪያ ምፅአቱ ለእስራኤል መንግስትን የሚመልስ የይሁዳ አንበሳ ሆኖ ሳይሆን የተገለጠው የአለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ነው የተገለጠው። በሁለተኛው ምፅአቱ ደግሞ የዳዊትን መንግስት የሚመልስ የይሁዳ አንበሳ ሆኖ ይገለጣል።

የሉቃስ ወንጌል 1:32 (AMH)

32 እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል፥ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤

የሺኛው መንግስትን አላማ ሲያብራሩት ምድር ገነት ትሆናለች ይላሉ። ምድር


GFX By: AD Graphics | +251916698510

ወደነበረችበት ሁኔታ ትመለሳለች። አሁን ምድር ስለተረገመች ይችህኛው የተረገመችው ምድርን ለማደስ ነው ይላሉ። እንደዚህ ብለው የሚያምኑት በምድር ሳይሆን በሰማይ ነው ለዘለዓለም የምንኖረው ብለው ስለሚያምኑ ነው። ምድር ትጠፋለች ብለው ያምናሉ። በሺኛው ዘመን ኢየሱስ የእራሱን ቤተመቅደስ ይሰራል ይላሉ። በእዚህኛው መቅደስ ውስጥ አገልጋዮች ይኖራሉ ብለው ያምናሉ። የማያምኑ ሰዎች በምድር ላይ ይኖራሉ ባልተለወጠ ስጋቸው፣ በኢየሱስ የሚያምኑ እስራኤላውያንም ስጋቸው ሳይለወጥ ይኖራሉ። ቤተክርስቲያን ደግሞ የሚኖሩት በትንሣኤ አካላቸው ነው ይላሉ። የሚያምኑ ሰዎች ኢየሱስ በሚያወጣው የመተዳደሪያ ደንብ ነው። ቢተላለፉ ግን ይቀጣሉ።

የሺኛው መንግስት የሚጠቃለልበት ጊዜ ይመጣል። ሊጠናቀቅ ሲሌ ሰይጣን ይፈታል፣ ጎግ እና ማጎግን አመፀኛ አድርጎ ያስነሳል። ሰዎችን ያስተባብራል ከእዚያ ጦሩን አሰልፎ ወደ ኢየሩሳሌም ይመጣል።

## PREMILLENNIALISM መፅሐፍ ቅዱሳዊ ነው?

በአጭሩ አይደለም። ይህ ምልከታ መፅሐፍ ቅዱሳዊ እንዳልሆነ ለማብራራት እንሞክር።

1ኛ, ስለዘመን መጨረሻ የሚናገሩ በርካታ ምንባባት ኖሮ እንዴት በዮሐንስ ራዕይ ብቻ ስለ ሺኛው መንግስት ይናገራል? ይህም ክፍል የሚገኘው ተምሳሌታዊነት በሚበዛው በራዕይ መፅሐፍ ነው።

ይህው የሺኛውን መንግስት የሚያወራው ክፍል በራሱ በተምሳሌታዊ አገላለጽ የታጨቀ ነው። ለምሳሌ፡ እዛያ ቀጥር ላይ እንኳን ተምሳሌታዊ አገላለጽ እናገኛለን።

**ራእይ 20:1**

> 1 የጥልቀንም መክፈቻና ታላቅን ሰንሰለት
> በእጁ የያዘ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ።

መክፈቻ ሲል የምርም እንደ ቁልፋ ያለ ነገር ይዟል እያልን አይደለም። ይህንን አገላለጽ ለኢየሱስ ይጠቀማል።

**የዮሐንስ ራእይ 1:18**

> የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ።

2ኛ, ይህንን ክፍል ጥሬውን የምንተረጉም ከሆነ በራዕይ 20 መሰረት ሁለት ትንሳኤ ነው የተገለፁት። እንደ premillennial አስተሳሰብ ሁለቱ ትንሳኤ 1ኛው ትንሳኤ ከ "ሺ" ኛው አመት በፊት የቅዱሳን ትንሳኤ የሚሆን ሲሆን ፤ 2ኛው, ደግሞ ከሺኛው አመት በኋላ የማያምኑ ሰዎች ትንሳኤ ነው።

እዚህ ጋር ዋናው ጥያቄ በሰባቱ አመት የከራው ጊዜ እና በ ሺኛው መንግስት አምነው የሚሞቱ ሰዎች እንዳሉም ያምናሉ። ይህ ከሆነ የእነዚህ አማኞች ትንሳኤ መቼ ነው የሚሆነው? ምክንያቱም Already ሁለቱ ትንሳኤ ተዘግበዋል።

3ኛ, የPremillennial ትልቁ ችግር የ ሺኛው መንግስት ትኩረት የሚያደርገው ቤተክርስቲያንን ሳይሆን እስራኤልን ነው። ስለዚህ እና አማኞች ይህ ሺኛው መንግስት ተስፋችን ሊሆን አይችልም። እንደውም እንሱ እንደሚሉት ከሆነ ለእና ከሺኛው መንግስት ይልቅ ለሰባት አመት መሰማይ መሆኑ ይሻለናል። ከእዛ ወርዶ ካላመኑ ሰዎች ጋር 1000 አመት ከመኖር እጅግ ይሻለናል።

4ኛ, ኢየሱስ ለወደፊት የምንጠብቀው ንጉሥ ሳይሆን already ነግሷል። ከእዚህ በኋላ የኢየሱስን አገዛዝ መገለጥ በሙላት ነው የምንጠብቀው እንጂ እንደ አዲስ ይመግሳል ብለን አንጠብቅም።

**የሐዋርያት ሥራ 2:36-37**

> 36 አለ። እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ። 37 ይህንም በሰሙ ጊዜ ልባቸው ተነካ፥ ጴጥሮስንና ሌሎችንም ሐዋርያት። ወንድሞች ሆይ፥ ምን እናድርግ? አሉአቸው።

በመሰረቱ እና ስናምን ምን ብለን ነው የመነው? ኢየሱስ ጌታ ነው ፣ ንጉሳችን



GFX By: AD Graphics | +251916698510

ነው ብለን ነው የመንነው:: ይህን ሮሜ 10:9 ላይ እናገኛለን::

**ሮሜ 10፥9 (አዲሱ መ.ት)**

""ኢየሱስ ጌታ ነው" ብለህ በአፍህ ብትመሰክር፣ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን፣ ትድናለህ::"

5ኛ, የማያምኑ እና የሚያምኑ ሰዎች አካለዊ ትንሳኤቸው በተመሳሳይ ጊዜ ነው የሚሆነው::

**የሐንስ 5 (አዲሱ መ.ት)**

28 "በዚህ አትደነቁ፤ መቃብር ውስጥ ያሉ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ጊዜ ይመጣል፤ 29 መልካም የሠሩ ለሕይወት ትንሣኤ፣ ክፉ የሠሩ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉ::

ኢየሱስ በታቅ መለከት በሚመጣበት ጊዜ ድምፁን ሲየሰማ የንቀላፋት ሁሉ አማኝ የሆነም አማኝ ያልሆነም ከሙታን ይነሳሉ::

**ዳንኤል 12 (አዲሱ መ.ት)**

1 "በዚያን ዘመን ስለ ሕዝብህ የሚቈመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል:: መንግሥታት ከተመሠረቱበት ጊዜ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ ታይቶ የማይታወቅ ታላቅ የመከራ ጊዜ ይሆናል:: ነገር ግን በዚያን ጊዜ ስማቸው በመጽሐፉ ተጽፎ የተገኘው ሕዝብህ ሁሉ ይድናሉ:: 2 በምድር ዐፈር ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎች ይነቃሉ፤ አንዳንዶቹ ለዘላለም ሕይወት፣ ሌሎቹም ለውርደትና ለዘላለም ንስቍልና ይነሣሉ::

እንዴት ነው በከበረ አካል ያሉት ፍፁማን ቅዱሳን በስጋ ካሉት ኃጢአተኞች ጋር ህብረት የሚኖራቸው? ይህንን ማሰብ ከባድ ነው:: ክርስቶስ የኔ በአካል በሺኛው መንግስት ለመንገስ ሲመጣ እንዴት ነው የኔ ሰዎች አንቀበልህም ሊሉት የሚችሉት? እንዴትስ ነው ከእርሱ ጋር ለመዋጋት የሚያስቡት?

## POSTMILLENNIALISM

# ድህረ ሺ አመት

(ከሺው አመት መንግስት በኋላ ክርስቶስ ይመጣል)

---

ኢየሱስ የሚነግሰው በመንፈሳዊ ሁኔታ ነው:: ይህም የሚሆነው በቤተክርስተየን በኩል ነው::

በሺኛው ዘመነ መንግስት የወንጌሉ መስፋት እና የቤተክርስተየን እድገት ቀስ በቀስ ይጨምራል:: በእዚህም እጅግ ብዙ የሆነው የአለም ክፍል ክርስቲየን ይሆናሉ:: በእዚህም የማህበረሰቡ ህይወት እየተለወጠ ሰላም እና ፅድቅ በምድር ላይ ይሰፍናል ይላሉ:: ኢየሱስ የሚነግሰው በመንፈሳዊ ሁኔታ ነው:: ግን በቤተክርስተየን በኩል ነው::

**የማቴዎስ ወንጌል 13:31-32 (NASV)**

31 ሌላ ምሳሌ እንዲህ ሲል ነገራቸው፤ "መንግሥተ ሰማይ አንድ ሰው ወስዶ በዕርሻው ቦታ የዘራትን የሰናፍጭ ዘር ትመስላለች:: 32 የሰናፍጭ ዘር ከሌሎች ዘሮች ሁሉ የነሰች ብትሆንም፣ ስታድግ ግን ከቍጥቋጦዎች ሁሉ በልጣ፣ የሰማይ ወፎች መጥተው በቅርንጫፎቿ ላይ እስኪያርፉ ድረስ ዛፍ ትሆናለች::"

ማቴ 28:18 በመጠቀም ክርስቶስ በሰማይ እና በምድር ስልጣን ስላለው እና እስከ አለም ፍፃሜ ከእኛ ጋር ስለሚሆን አለምን ደል እንደምንቀዳጅ እንጠብቃለን::

ሌላኛው ማቴ 16 ላይ የገሃነም ደጆች አይችሏትም የሚለውን በመጠቀም:: የሮም ከተሞች ሲገነቡ እራሳቸውን ለመከላከል በዙሪያቸው ቅጥርን ይቀጥራሉ:: ጠላት ከሌለ ለእራሳቸው መግቢያና መውጫ እንዲሆን፣ ጠላት


GFX By: AD Graphics | +251916698510

ካለ ደግሞ በራቸውን ጥርቅም አድርገው ዘግተው እራሳቸውን ለመከላከል ይጠቀሙበታል፡፡

ወራሪው ጠላት የከተማውን በር ሰብሮ እስኪገባ ይዋጋሉ፡፡ ጠላቶቻቸው ካሸነፉቸውም በሮቻቸውን ያቃጥላሉ፡፡ ኢየሱስ ይህንን ምሳሌ በመጠቀም ቤተክርስቲያንን የገሀነም ደጆች አይችሏትም ተብሏል፡፡ ቤተክርስቲያን እራሷን ከጠላት ወረራ የምትከላከል ሳይሆን ወደ ገሀነም ደጆች ጦሯን ይዞ ወረራ አድርጋ የገሀነም ደጆችን የምታንቀጠቅጥ እንጂ ገሀነም የሚያንቀጠቅጣት ደካማ አለመሆኗን ገልጿል፡፡

ስለዚህ በእዚህ ምድር ቆይታዋ ቤተክርስቲያን እየሰፋች በእዚህ ምድር ላይ ሰላም እና መረጋጋት እየሰፈነ ይመጣል የሚል ድምዳሜ አላቸው፡፡

ይህ አመለካከት ከሌሎች የመፅሐፍ ቅዱስ ምንባባት ጋር ይጋጫል

### የማቴዎስ ወንጌል 7:13-14

[13] “በጠባቡ በር ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው መንገድ
ትልቅ፣ በሩም ሰፊ ነውና፤ ብዙዎችም በዚያ ይገባሉ፡፡ [14] ወደ
ሕይወት የሚያደርሰው ግን መንገዱ ቀጭን፣ በሩም ጠባብ
ነው፤ የሚገቡበትም ጥቂቶች ብቻ ናቸው፡፡

### የሉቃስ ወንጌል 18:8

የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ በምድር ላይ እምነትን ያገኝ ይሆንን?”

ይህ ጥያቄ ምድር በሚያምኑ ሰዎች የምትሞላ ሳይሆን እምነት የሌላቸው እንደሚበዙ የሚጠቀም ነው፡፡

### 2ኛ ጢሞቴዎስ 3 (አዲሱ መ.ት)

[1] ነገር ግን በመጨረሻው ዘመን የሚያስጨንቅ ጊዜ
እንደሚመጣ ይህን ዕወቅ፡፡ [2] ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ
ይሆናሉ፤ ገንዘብን የሚወዱ፣ ትምክሕተኞች፣ ትዕቢተኞች፣
ተሳዳቢዎች፣ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ የማያመሰግኑ፣
ቅድስና የሌላቸው፣ [3] ፍቅር የሌላቸው፣ ለዕርቅ የማይሸነፉ፣
ሐሜተኞች፣ ራሳቸውን የማይገዙ፣ ጨካኞች፣ መልካም
የሆነውን የማይወዱ፣ [4] ከዳተኞች፣ ችኩሎች፣ በከንቱ
በትዕቢት የተወጠሩ፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን
የሚወዱ ይሆናሉና፡፡ [5] ሃይማኖታዊ መልክ አላቸው፤ ኃይሉን
ግን ክደዋል፡፡ ከእነዚህ ራቅ፡፡ … [12] በርግጥም በክርስቶስ
ኢየሱስ በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት መኖር የሚወዱ
ሁሉ ይሰደዳሉ፡፡ [13] ክፉዎችና አታላዮች ግን እየሳቱና እያሳቱ፣
በክፋትም ላይ ክፋት እየጨመሩ ይሄዳሉ፡፡

## AMILLENNIALISM

# አልቦ ሺ አመት

---

Amillennialism ከሚለው ይልቅ ስያሜው symbolic Millennialism ቢባል የቸሻለ ነው፡፡ ሀሳቡን ግን እንገዛዋለሁ፡፡ Amillennialism ማለት፦ (no Millennialism) ሺኛው መንግስት የሚባል የለም ማለት ነው፡፡ ሺኛው መንግስት በዮሐንስ ራዕይ 20 ተገልጿል፡፡

የሺኛው መንግስት አመት አፈፃፀም በምድራዊ መንግስት ሳይሆን አሁን ባለው በክርስቶስ መንፈሳዊ መንግስት ነው ብሎ ማመን ነው አልቦ ሺ አመት፡፡ ሺ አመት የሚለው literal አንወስድም፡፡ ታዲያ ሺ አመት ሲባል ምን ማለት ነው? ቀጥታ የማንወስደው ከሆነ … በአቡ ቀለምሲሳዊ ፅሁፍ ውስጥ ብዙ ጊዜ 1000 የሚለው ቁጥር ረጅም፣ ሰፊ የሚለውን የሚገልጽ ነው፡፡ ለምሳሌ ዳንኤል ንጉሱን ንጉሥ ሆይ ሺ አመት ንገስ ሲል ፦ በጥሬው ወስደነው 1000 አመት ንገስ እያለው ነው አንልም፡፡ ምክንያቱም ሺ አመት ኖሮ የሚያውቅ ሰው የለም፡፡ ረጅም አመት ንገስ ለማለት ነው፡፡



GFX By: AD Graphics | +251916698510

መዝሙር ዳዊት 90:4

> 4 ሺህ ዓመት በፊትህ እንዳለፈች እንደ ትናንት ቀን፥ እንደ ሌሊትም ትጋት ነውና።

ዳዊት በእኛ ዘመን ሆኖ ቢሆን ኖሮ እንዳለፈች እንደ ዛሬ ሰኮንድ ናት ይል ነበር። ምክንያቱም በጣም ቅርብ የሆነን ነገር ለመግለጽ የሚያገለግል ስለሆነ።

መዝሙር ዳዊት 105:8

> [8] ቃል ኪዳኑን ለዘላለም፥ እስከ ሺህ ትውልድ ያዘዘውን ቃሉን አሰበ፥

እዚህ ጋር በቀጥታ 1000 የሚለውን ወስደነው ከአንድ ሺ አመት በኋላ ያለው ትውልድን አይመለከትም ማለት አይደለም። የእግዚአብሔርን ቃልኪዳን እና ያዘዘውንም ቃሉን ሁሉጊዜ ሊታወስ ይገባል። ስለዚህ ረዥም ጊዜን ፣ ሰፊ ጊዜን ለመግለጽ ነው ሺ የሚለውን ቁጥር የተጠቀመው።

> የእግዚአብሔር መንግስት ለወደፊት የምትመጣ ናት ወይንስ በመካከላችን ናት?

የማቴዎስ ወንጌል 12:28

> [28] እኔ ግን በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ፥ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ደርሳለች።

የሉቃስ ወንጌል 17:20-21

> [20] ፈሪሳውያንም። የእግዚአብሔር መንግሥት መቼ ትመጣለች ብለው ቢጠይቁት፥ መለሰ። የእግዚአብሔር መንግሥት በመጠባበቅ አትመጣም፤O[21] ደግሞም። እንኋት በዚህ ወይም። እንኋት በዚያ አይሉአትም። እነሆ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናትና አላቸው።

ስለዚህ ለወደፊት የምንጠብቀው የሺ አመት መንግስት የለም። በመጀመሪያው መፅአቱ እና በሁለመናው ምፅአቱ መካከል ያለውን ጊዜ ሁሉ ነው ሺኛው መንግስት የምንለው።

በሺኛው መንግስት ጊዜ ምን ይሆናል?

> 1ኛ, ሰይጣን ይታሰራል
> 2ኛ, የመጀመሪያው ትንሳኤ ይካሄዳል
> 3ኛ, አማኞች ከክርስቶስ ጋር ይነግሳ

## ◆ ሰይጣን ይታሰራል

ሰይጣን መቼ ታሰረ? ሰይጣን ታሰረ ማለትስ ምን ማለት ነው? የሰይጣን የታሰረው በምዕራፍ 12 ላይ ነው።

የዮሐንስ ራእይ 12:10-11

> [10] ታላቅም ድምፅ በሰማይ ሰማሁ እንዲህ ሲል። አሁን የአምላካችን ማዳንና ኃይል መንግሥትም የክርስቶስም ሥልጣን ሆነ፥ ቀንና ሌሊትም በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአልና። [11] እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት፥ ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም።

የሰይጣን መታሰር ሰይጣንን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ሳይሆን በኢየሱስ ትንሳኤ አማካኝነት የእግዚአብሔር መንግስት አህዛብን ከሰይጣን መንግስት ፈልቅቆ ማውጣቱ ነው።

የማርቆስ ወንጌል 3:27

> [27] ነገር ግን አስቀድሞ ኃይለኛውን ሳያስር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ ዕቃውን ሊበዘብዝ የሚችል የለም፥ ከዚያም ወዲያ ቤቱን ይበዘብዛል።

ከእዚህ በኋላ የሚሸነፍ አዲስ ሰይጣን የለም። Already በኢየሱስ ሞት እና ትንሳኤ አማካኝነት ሰይጣን ተሸንፏል።


GFX By: AD Graphics | +251916698510

## ◆ የመጀመሪያው ትንሳኤ ይባላል

የፊተኛው ትንሳኤ የሚለው፡- መንፈሳዊ ትንሳኤ ወይንም የአማኞች አዲስ ህይወት ነው፡፡ ሮሜ 6 ላይ እንዳለው፡፡

ሮሜ 6 (አዲሱ መ.ት)

4 ስለዚህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሞት እንደ ተነሣ፣ እኛም
እንዲሁ በአዲስ ሕይወት እንድንኖር በጥምቀት ሞተን
ከእርሱ ጋር ተቀብረናል፡፡ 5 በሞቱ ከእርሱ ጋር እንዲዚህ
ከተባበርን፣ በትንሣኤው ደግሞ በርግጥ ከእርሱ ጋር
እንተባበራለን፡፡ ...11 እንደዚሁም ለኀጢአት እንደ ሞታችሁ፣
ነገር ግን በክርስቶስ ኢየሱስ ለእግዚአብሔር ሕያዋን
እንደሆናችሁ ራሳችሁን ቍጠሩ፡፡

የሐንስ 5 (አዲሱ መ.ት)

24 "እውነት እላችኋለሁ፤ ቃሌን የሚሰማ፣ በላከኝም
የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ ከሞት ወደ ሕይወት
ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም፡፡ 25 እውነት እላችኋለሁ፤
ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ጊዜ
ይመጣል፤ አሁንም መጥቶአል፤ የሚሰሙትም በሕይወት
ይኖራሉ፡፡

ይህንን አይነት አገላለጽ ኤፌሶን 2 ለይ፣ ሉቃስ 15 ላይ እናገኛለን፡፡

## ◆ አማኞች ከክርስቶስ ጋር ይነሳሉ

አማኞች በክርስቶስ በመሆናቸው ምክንያት አሁን ላይ ነግሰዋል፡፡

ኤፌሶን 1 (አዲሱ መ.ት)

20 ክርስቶስን ከሙታን ሲያስነሣውና በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ
ሲያስቀምጠው የታየው ነው፡፡ 21 የተቀመጠውም ከግዛትና
ከሥልጣን፣ ከኀይልና ከጌትነት እንዲሁም በአሁኑ ዘመን ብቻ
ሳይሆን በሚመጣውም ዘመን ቢሆን ሊሰየም
ከሚቻለው ስም ሁሉ በላይ ነው፡፡

ኤፌሶን 2፡6 (አዲሱ መ.ት)

"እግዚአብሔርም ከክርስቶስ ጋር አስነሣን፤ በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን፤"

ይህ መወደቅን የሚያመለክት ሳይሆን ከዙፋን ፣ ከመንገስ ጋር አብሮ ተያይዞ የሚነሳ ቃል ነው፡፡ ማለትም በዙፋን ላይ መቀመጥን የሚያሳይ ነው፡፡ ስለዚህ ነገስታተ አድርጎናል፡፡

የዮሐንስ ራእይ 5:9 (AMH)

9 መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ ማኅተሞቹንም ትፈታ ዘንድ
ይገባሃል፥ ታርደሃልና፥ በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ
ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን
ዋጅተህለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ
አደረግሃቸው፥ በምድርም ላይ ይነግሣሉ እያሉ አዲስን ቅኔ
ይዘምራሉ፡፡

በእዚህ አገላለጽ አማኞች ካህናትም ናቸው መንግስትም ናቸው፡፡ ካህናት እና መንግስት የሚሆኑት ነገር ሳይሆን የሆኑት ነገር ነው፡፡ የግዛቱ በቤተክርስቲያን ዘመን ውስጥ ቀድሞውኑ ተጀምሯል ነግርግን Final fulfillmentን እንጠብቃለን፡፡

የማቴዎስ ምዕራፍ 24 እና 25 በጣም ብዙ ትርጉሞች የተሰጡበት ክፍል እና ለመረዳት ፈታኝ የሆነ ክፍል ነው፡፡ ምዕራፍ 24 እና 25 የኢየሱስ የመጨረሻው ትምህርት ነው፡፡ ይህንን የማቴዎስ 24 ን በተመለከተ የተለያዩ ምልከታዎች አሉበት፡፡

**1ኛ, Preterists፦** ሁሉንም ትንቢቶች በ 70 AD ተፈፅመዋል ብለው የምናሉ፡፡ የPreterists ዋና ሙግታቸው ቁጥር 34 ነው፡፡ ይህ ትውልድ አያልፍም የሚለው ነው፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ የተናገራቸው ነገሮች

የተፈፀሙት በእዚያው ዘመን የተፈፀመ አንንጂ ለወደፊቱ የምንጠብቀው አይደለም። ይህንን ሲሉ ግን የማቴዎስ 24 ላይ ያለውን ብቻ ሳይሆን በሙሉ በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ ያለውንም ትንቢቶች ጨምሮ ነው።

**2ኛ, Futurist** (especially Dispensational Premillennialists ደግሞ፦ ማቴዎስ 24 ሙሉ በሙሉ ወደፊት የሚፈፀም ነው እንጂ እኛ ስንመለከተው ወደኋላ የተፈፀመ አንዳች ነገር የለም ይላሉ።

**3ኛ, Partial Preterists** ደግሞ ማቴዎስ 24 በ70 AD የተፈፀሙትንም ይዟል፣ ወደፊት የሚፈፀሙ ነገሮችንም ይዟል።

**4ኛ, Double Fulfillment** "Already–Not Yet" የሚሉት ነው። Already የተከናወነ ነው የሚሉት። በ AD 70 የተፈፀመው Judgment ነው። Not yet የሚሉት ደግሞ final judgmentን ነው የሚያመለክተው ይላሉ። 70 AD shadow ሆኖ ስለ final judgment የሚያብራራ ነው ይላሉ። ስለዚህ በአንድ ጊዜ ሁለት ነገሮችን እያወራ ነው ይላሉ።

ከእነዚህ ምልከታዎች መፅሐፍ ቅዱሳዊው የሆነው የትኛው ነው?

ይህንን የክፍሉን ሀሳብ በጥንቃቄ በመመልከት ወደ አንድ ድምዳሜ እንድረስ። ማቴዎስ 24 ከማርቆስ 13 እና ከሉቃስ 24 ጋር አብሮ ቢታይ ጥሩ ነው። ቀጥር በቀጥር እያብራራን የምንሄድ ቢሆን እያንዳንዱን ቀጥር ከማርቆስ ጋር እና ከሉቃስ ጋር እያስተያየን እንመለከት ነበር። ነገርግን በእዚህ ትምህርታችን ዳሰሳ ነው እንጂ የምናደርገው ሙሉ በሙሉ አንመለከተውም።

የእዚህ የማቴዎስ 24 አውድ ከምዕራፍ 22 ነው የሚጀምረው። ከእዛ እስከ ምዕራፍ 25 ይቀጥላል። ስለዚህ ማቴዎስ 24ን ስናጠና ከ22 ጀምሮ እስከ 25 ድረስ መመልከቱ ወሳኙ ነው።

ምዕራፍ 22 እና 23 በዋናነት ሁለት ነገሮችን ይነግረናል።

1, እስራኤል እንደምትተው እና መንግስት ከእስራኤል እንደሚወሰደ ያወራል። ይህንን አንድ ገበሬ የወይኑን ቦታ ለአተክልተኞች አከራይቶ በሄደበት ምሳሌ መመልከት እንችላለን።

2, እስራኤላውያን ላይ ፍርድ እንደሚመጣ ይናገራል።

የማቴዎስ ወንጌል 23:35-38 (NASV)

35 ስለዚህ፣ ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ በመቅደሱና
በመሠዊያው መካከል እስከ ገደላችሁት እስከ በራክዩ
ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ፣ በምድር ላይ ለፈሰሰው
ንጹሕ ደም ሁሉ እናንተ ተጠያቂዎች ናችሁ። 36 እውነት
እላችኋለሁ፤ ላለፈው ነገር ሁሉ ይህ ትውልድ ይጠየቅበታል።
37 "አንቺ ነቢያትን የምትገድዪ፣ ወደ አንቺ የተላኩትንም
በድንጋይ የምትወግሪ ኢየሩሳሌም ሆይ፤ አንቺ ኢየሩሳሌም!
ዶሮ ጫጩቶቿን በክንፎቿ ሥር እንደምትሰበስብ፣ ልጆችሽን
ለመሰብሰብ ስንት ጊዜ ፈለግሁ! እናንተ ግን ፈቃደኛ
አልሆናችሁም፤ 38 እነሆ፤ ቤታችሁ ወና ሆኖ ይቀርላችኋል!

ይህ ምዕራፍ እንዳለቀ ነው የምዕራፍ 24 ሀሳብ የሚጀምረው። ማቴዎስ 24 ላይ 3 ጥያቄዎች ነው የተጠየቁት ለሶስቱ ጥያቄዎች እስከ ምዕራፍ 25 ድረስ ኢየሱስ መልስ ሰጥቷል።

1ኛ, የመቅደሱ መፍረስ፣
2ኛ, የክርስቶስ መምጣት እና
3ኛ, የዘመን መጨረሻ ምልክቶች ናቸው።

የዘመን መጨረሻ ሳይሆን ጥያቄዎች የዘመን መጨረሻ ምልክቶችን ነው የጠየቁት። ለእዛ ነው መልክቶችን ከዘረዘረ በኋላ መጨረሻው ገና ነው ያላቸው።

ግን እነዚህ መልሶች በቀጥር ከፋፍለን ከእዚህ እስከእዚህ እያልን ነው



GFX By: AD Graphics | +251916698510

የምንረዳው? ወይንም ተደበላልቆ ነው የተቀመጠው? በሁለቱም መንገድ የሚረዱ አሉ፡፡

ተደበላልቆ ነው የተቀመጠው፡፡ ከእዚህ እስከ እዚህ ስለዚህ ነገር ያወራል ማለት አንችልም፡፡

የማቴዎስ 24ን ሙሉውን ሀሳብ መመልከት ባንችልም በዋናነት የምንመለከታቸው 7 ነገሮች ናቸው፡፡

1. የመንግስቱ ወንጌል ለአለም ሁሉ ይሰበካል፡፡
2. ታላቅ መከራ
3. ጨረቃ ኳክብት ይረግፋሉ የሚለው በቀጥታ የሚወሰድ አይደለም፡፡
4. ይህ ትውልድ አያልፍም
5. ሰማይና ምድር ያልፋሉ፡፡
6. ከአብ በቀር ልጅም ቢሆን አያውቅም
7. የአህዛብ ዘመን (ይህንን ቀጣይ ሳምንት እንመለከተዋለ) የመንግስቱ ወንጌል ለአለም ሁሉ ይሰበካል

### ቁጥር 24

“ለሕዝብ ሁሉ ምስክር እንዲሆን፣ ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፤ ከዚያም መጨረሻው ይመጣል፡፡”

የመንግስቱ ወንጌል ለአለም ሁሉ ይሰበካል ሲል ስለየትኛው አለም ነው የሚያወራው?

ብዙ ሰዎች የሚተረጉሙት፦ ይህ የሚታየው የሰው ልጆች ሁሉ የሚኖሩበትን አለም ነው የሚያስቡት፡፡ ነገርግን ኢየሱስ እየተናገረ ያለው እነሱ ስለሚናገሩት አለም ነው ወይ? ብለን መጠየቅ አለብን፡፡

ጌታችን ኢየሱስ እየተናገረ ያለው አለም በእዚያን ዘመን ስለነበረው አለም ነው፡፡ በሮም መንግስት ስር ስለነበረው ሰለ Roman Empire ነው፡፡

### የሉቃስ ወንጌል 2:1 (NASV)

1 በዚያን ዘመን፣ የዓለሙ ሁሉ ሕዝብ እንዲቈጠርና እንዲመዘገብ ከአውግስጦስ ቄሳር ትእዛዝ ወጣ፡፡

### ሮሜ 1:8 (NASV)

8 ከሁሉ አስቀድሜ፣ እምነታችሁ በዓለም ሁሉ በመሰማቱ፣ ስለ ሁላችሁ አምላኬን በኢየሱስ ክርስቶስ አመሰግናለሁ፡፡

### የሐዋርያት ሥራ 17:6 (NASV)

6 ነገር ግን ሊያገኟቸው አልቻሉም፤ ስለዚህ ኢያሶንንና ሌሎች ወንድሞችን በከተማው ባለ ሥልጣናት ፊት እየጐተቷቸው እንዲህ እያሉ ጮኹ፤ “እነዚህ ሰዎች ዓለሙን ሁሉ ሲያውኩ ቈይተው፣ አሁን ደግሞ ወደዚህ መጥተዋል፤

### ቆላስይስ 1:6 (NASV)

6 ይህም ወደ እናንተ ደርሷል፡፡ ይህንም ወንጌል ከሰማችሁበትና የእግዚአብሔርን ጸጋ በእውነት ከተረዳችሁበት ቀን ጀምሮ በዓለም ዙሪያ እየሠራ እንዳለ ሁሉ በእናንተም ዘንድ ፍሬ እያፈራና እያደገ ነው፡፡

በኢየሩሳሌም ፣ በይሁዳ ፣ በሰማሪያ እና እስከ ምድር ዳርቻ ስበኩ የሚለው፦ በሮም ኢምፓየር ስላለው አለም ነው፡፡ በሜድትራንያን ዙሪያ ያለው ነው፡፡

ከእዛ በኋላ እየሰፋ ስለመጣው አለም እና እስከዛሬ እኛ ስለምንኖርበት አለም እያወራ አይደለም፡፡ ለእዚህ አንዱ ማሳያ፦

### ቆላስይስ 1:23 (NASV)

23 ይህም የሚሆነው በእምነታችሁ ተመሥርታችሁና ተደላድላችሁ በመቆም ከሰማችሁት የወንጌል ተስፋ ሳትናወጡ ጸንታችሁ ብትኖሩ ነው፡፡ እናንተ የሰማችሁትና ከሰማይ በታች ላለ ፍጥረት ሁሉ የተሰበከውም ወንጌል ይኸው ነው፤ እኔም ጳውሎስ ለዚህ ወንጌል አገልጋይ ሆንሁ፡፡



GFX By: AD Graphics | +251916698510

መፅሐፍ ቅዱስ to us አልተፃፈም፣ ነገር ግን for us ተፅፏል። to us አልተፃፈም ማለት በቀጥታ ለቆሮንቶስ ሰዎች እንደተፃፈ ለእኛ አልተፃፈም። ነገርግን finally እኛ እንድንጠቀምበት ነው።

# ታላቁ መከራ

## የማቴዎስ ወንጌል 24

21 በዚያን ጊዜ፣ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ
ሆኖ የማያውቅ፣ ከዚያም በኋላ የሚስተካከለው የሌለ፣
ታላቅ መከራ ይሆናል።

ይህንን text በመያዝ dispensationalኦች ይህ ታላቀ መከራ ከቤተክርስቲያን ንጥቀት በኋላ ባላመኑ ሰዎች ላይ የሚሆነው መከራ ነው ይላሉ። ነገርግን ማቴዎስ በ19ኛው መቶ ክፍለዘመን የተነሳውን የDispensationalኦችን Concept ይዞ አይደለም ይህንን የፃፈው።

ታድያ ይህ ታላቀ መከራ የሚለው ስለ የትኛው ነው?

በ 70 AD የተፈፀመውን ጭፍጨፋ ታሳቢ አድርጎ ነው።

ይህ ስለ 70 AD እያወራ ከሆነ በሁለተኛው የአለም ጦርነት ወደ 6 ሚሊዮን ገደማ የሚሆን አይሁዳዊ በሂትለር ተገድለዋል። ታዲያ ያ በ 70 AD ከደረሰው የከፋ አይደል? ይላሉ።

ነገርግን መታየት ያለበት በዘመኑ ከነበረው ከህዝቡ ቁጥር አንፃር ነው። በመጀመሪያው ክፍለዘመን ከነበረው የአይሁድ ቀጥር አንፃር ብዙ ነው። በሂትለር ጊዜ ከተጨፈጨፈው አንፃር ሲታይ የመጀመሪያው ይበዛል የሚሉም አሉ።

የጌታን ዳግም ምፅአት ነው የሚያመለክተው ካልን ከእዚያ በኋላ መከራ ይቀጥላል ማለት ነው? ለእኔ የተሻለው በጣም ከባድ መከራ እንደሚመጣ ለመግለጽ figure of speach ነው።

እስራኤል ነፍሳቸውን ማትረፍ ከፈለጉ ከኢየሩሳሌም እንዲወጡ አስጠንቅቋቸው ነበር። የማቴዎስ ወንጌል

## 24:15-20 (NASV)

15 “እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተነገረው፣ ‘የጥፋት ርኩሰት’
በተቀደሰው ስፍራ ቆሞ ስታዩ፣ አንባቢው ያስተውል። 16
በዚያን ጊዜ በይሁዳ የሚገኙ ወደ ተራራዎች ይሽሹ፤ 17 በቤቱ
ጣራ ላይ የሚገኝ ማንም ሰው ዕቃውን ከቤቱ ለማውጣት
አይውረድ፤ 18 በዕርሻ ቦታው የሚገኝ ማንም ሰው ልብሱን
ለመውሰድ አይመለስ። 19 በእነዚያ ቀናት ለነፍሰ ጡሮችና
ለሚያጠቡ ወዮላቸው! 20 እንግዲህ ሽሽታችሁ በክረምት
ወይም በሰንበት ቀን እንዳይሆን ጸልዩ፤

ይህንን ሉቃስ አብራርቶታል።

## የሉቃስ ወንጌል 21:20-22

20 “ኢየሩሳሌም በጦር ሰራዊት ተከብባ በምታዩበት ጊዜ፣
ጥፋቷ መቃረቡን ዕወቁ። 21 በዚያን ጊዜ በይሁዳ ያሉ ወደ
ተራሮች ይሽሹ፤ በከተማ ያሉትም ከዚያ ይውጡ፤ በገጠር
ያሉትም ወደ ከተማዪቱ አይግቡ፤ 22 የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም
ዘንድ ይህ የበቀል ጊዜ ነውና።

አይሁድ ኢየሱስን በሰቀሉበት በ37ኛው አመት የፋሲካን በአል ለማክበር ከተለያየ የአለም አአቅጣጫ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ አይሁዳውያን በኢየሩሳሌም ተሰብስበዋል። ነገርግን ቄሳር ቲቱስ ኢየሩሳሌምን ለማጥፋት ተዘጋጅቶ ነበር። ከ60 ሺ በላይ ጦር ፣ ተወርዋሪ የድንጋይ መተኮሻዎች እና ፈረሰኞች ኢየሩሳሌምን መክበብ ጀመሩ። ሮማዊያን ማንም ከከተማይቱ እንዳያመልጥ ጠንካራ ቅጥርን ሰርተው ነበር። በእስራኤልም ላይ ከባድ ጦራቸውን አራገፉባቸው። በእዚህም ብዙዎቹ ሞቱ። በእዚህም ጦርነት በእረሃብ እበት እና ቁርበት ያገኙትንም ይበሉ ነበር። እንደውም የአይሁድ የታሪክ ፀሐፊ ጆሴፈስ እንደሚለው እናት ልጇን ቀቅላ በልታለች ይላል።


GFX By: AD Graphics | +251916698510

ጆሴፈስ እንደዘገበው ወደ 1.1 ሚሊየን የሚቆጠሩ አይሁዳውያን በጦርነቱ እና ጦርነቱ በፈጠረው ረሃብ ምክንያት ሞተዋል ብሏል። 97 ሺ የሚጠጉ ደግሞ በምርኮ ተወስደው ተሸጠዋል።

ሰማንያ አመት የፈጀው መቅደስ ባለቀ በስድስት እና በሰባት አመት ውስጥ ነው የፈረሰው። ከባድ እና አሰቃቂ ፍርድ ነበር።

## ፀሐይ ትጨልማለች፤ ጨረቃ ብርሃኗን ትከለክላለች፤ ከዋክብት ከሰማይ ይረግፋሉ

የማቴዎስ ወንጌል 24

29 “ወዲያውኑ ከእነዚያ ከመከራው ቀናት በኋላ፣ “ ‘ፀሓይ ትጨልማለች፤ ጨረቃ ብርሃኗን ትከለክላለች፤ ከዋክብት ከሰማይ ይረግፋሉ፤ የሰማይ ኀይላትም ይናጋሉ።’

ይህ ክፍል ጥሬውን የሚተረጎም ነው? አይደለም። ለምሳሌ፦ ኢሳያስ ስለ ባቢሎን ወድቀት ሲናገር እንደዚህ ብሎ ነበር፦

ኢሳይያስ 13:10 (NASV)

10 የሰማይ ከዋክብትና ሰራዊታቸው፣ ብርሃን አይሰጡም፤ ፀሓይ ገና ከመውጣቷ ትጨልማለች፤ ጨረቃም ብርሃኗን አትሰጥም።

ህዝቅኤል ስለ ግብፅ ውድቀት ሲተነብይ፦

ሕዝቅኤል 32:7-8 (NASV)

7 አንተን በማጠፋ ጊዜ ሰማያትን እሸፍናለሁ፤ ከዋክብታቸውንም አጨልማለሁ፤ ፀሓይን በደመና እሸፍናለሁ፤ ጨረቃም ብርሃኗን አትሰጥም። 8 በሰማይ የሚያበሩትን ብርሃናት ሁሉ፣ በአንተ ላይ አጨልማለሁ፤ በምድርህ ላይ ጨለማን አመጣለሁ፤ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።

እነዚህ textኦች ስለ ፍርድ የሚያወሩ እንጂ ይህ ትንቢት በሙፈፀሙበት ጊዜ የምርም የተባሉት ነገር ተፈፅመዋል ማለት አይደለም። እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ምድር ሊያስወጣቸው ሲል በግብፅ ምድር ላይ የተደረገውን ያንን ፍርድ እንድያስታውሱ ነው ይህንን አይነት ምሳሌ የሚጠቀሙት።

## ይህ ትውልድ አያልፍም

“This generation”

የማቴዎስ ወንጌል 24

34 እውነት እላችኋለሁ፤ ይህ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም።

ይህ ትውልድ የሚለው አስቀድሞ በምዕራፍ 23 ተገልጿል።

የማቴዎስ ወንጌል 23:35-36 (NASV)

35 ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ በቤተ መቅደስና
በመሠዊያው መካከል እስከ ገደላችሁት እስከ በራክዩ ልጅ
እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ በምድር ላይ የፈሰሰው የጻድቅ
ደም ሁሉ ይደርስባችሁ ዘንድ። 36 እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ
ሁሉ በዚህ ትውልድ ላይ ይደርሳል። ሰማይና ምድር ያልፋሉ

የማቴዎስ ወንጌል 24

“ሰማይና ምድር ያልፋሉ፤ ቃሌ ግን ፈጽሞ አያልፍም።”

ሰማይና ምድር ሲል የትኛው ሰማይ እና ምድር? ይህ ጉኡዘ ሰማይ እና ምድር ፣ ቀና ስንል የሚታየውን ሰማይ በእግራችን የምንረግጠውን ምድር ነው? ወይንስ ሌላ ትርጉም አለው? ሰማይና ምድር ሲል አንድን kingdom ለመግለጥ የሚጠቀሙበት ቋንቋ ነው። የእዚህ የማቴዎስ 24 context ደግሞ ስለ እስራኤል መንግስት ማለፍ ነው የሚናገረው። በሙሴ ስርአት ሲተዳደር የነበረውን ብሉይ ኪዳናዊውን መንግስት ነው የሚያወራው። በአጭሩ ብሉይ ኪዳን አልፎ በአዲሱ ኪዳን እደሚተካ ነው የሚያወራው።

በእዚያን ዘመን የነበሩ **በመሶፖታሚያ** አከባቢ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ይጠቀሙበት



GFX By: AD Graphics | +251916698510

የነበረው የአነጋገር ስልት ነው።
ሰማይ እና ምድር የሚለው የእስራኤልን ህዝብ ለመግለጽ መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥቅም ላይ ውሏል።

**ኦሪት ዘዳግም 32:1 (NASV)**

1 ሰማያት ሆይ፤ አድምጡ፤ እኔም እናገራለሁ፤ ምድር ሆይ፤ አንቺም የአፌን ቃል ስሚ።

**ትንቢተ ኢሳይያስ 1:2 (NASV)**

2 ሰማያት ሆይ፤ ስሙ! ምድር ሆይ፤ አድምጪ! እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ተናግሯልና፤ "ልጆች ወለድሁ፣ አሳደግኋቸውም፤ እነርሱ ግን ዐመፁብኝ። ስለ እዚያች ሰአት ከአብ በቀር ልጅም ቢሆን አያውቅም

**የማቴዎስ ወንጌል 24፥36**

"ያን ቀንና ሰዓት ግን ከአብ በስተቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ፣ ወልድም ቢሆን ማንም አያውቅም።"

በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ቦታዎች ላይ ሁሉን አዋቂ መሆኑን ተገልጿል።

**ዮሐንስ 2 (አዲሱ መ.ት)**

24 ኢየሱስ ግን ሰውን ሁሉ ስለሚያውቅ፣ አይታመንባቸውም ነበር፤ 25 በሰው ውስጥ ያለውን ያውቅ ስለ ነበር፣

ማንም ስለ ሰው እንዲመሰክርለት አላስፈለገውም። ይህ ደግሞ የእግዚአብሔር ባህሪ ብቻ ነው።

**1ኛ ነገሥት 8፥39 (አዲሱ መ.ት)**

"በማደሪያህ በሰማይ ሆነህ ስማ፤ ይቅር በል፤ አድርግም። አንተ ብቻየሰውን ሁሉ ልብ የምታውቅ ስለ ሆንህ ልቡን ለምታውቀው ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ሥራው ሁሉ ክፈለው፤"

ታዲያ ወልድ ሁሉን አዋቂ ሆኖ ሳለ እንዴት ወልድም ቢሆን አያውቅም ይለናል?
እዚህ ክፍል ላይ ወልድን አያውቅም እያለ አይደለም። በአዲስ ኪዳናችን ላይ እውቀትን knowledge ለመግለጽ ኖሲስ የሚለውን የግሪክ ቃል ይጠቀማል። በእነዚህ ክፍሎች የተጠቀሰው የግሪክ ቃል ግን የተለየ ነው። οἶδεν (ኦኢደን) የሚል የግሪክ ቃል ነው። እንደ አገባቡ ማወጅ፣ ማሳወቅ/declare ማድረግ የሚለውን ይገልጻል። በእዚህ ክፍል ላይ ኢየሱስ ስለ አዕምሮ እውቀት አይደለም እያወራ ያለው።

**1ኛ ቆሮንቶስ 2፥2 (አዲሱ መ.ት)**

"በመካከላችሁ ሳለሁ ኢየሱስ ክርስቶስን ያውም የተሰቀለውን፣ እርሱን ብቻ እንጂ ሌላ እንዳላውቅ ወስኜ ነበርና።"

እዚህ ጋር ጳውሎስ ምንም ነገር አላውቅም እያለ አይደለም። ጳውሎስ እያለ ያለው አውዱን ከተመለከትን ከኢየሱስ መስቀል በቀር ሌላ ነገር ላላሳውቃችሁ ቆርሰጬ ነበር ነው። ማለትም በእዚያን ጊዜ ብዙ ፍልስፍና የሚወራበት የግሪክ ባህል ስለነበር ነው ይህንን ያለው።

ደግሞም በዘመኑ የነበረውን የአይሁድን ባህላዊ ነገር በሚያስታውሳቸው መልኩ እየገለፀ ነው።

በአይሁድ የሰርግ በአል መሰረት ሁለት ሰዎች እንዲጋቡ ስምምነት ከተደረገ በኋላ ወንዱ ሙሽራ ለሚስቱ አባቴ ቤት ሄጄ እቤት እሰራልሻለሁ ብሎ ቃል ይገባላትና እዛው ቤተሰቦቿ እቤት ትቷት ይሄዳል። ከእዛም ቤት መገንባት ይጀምራል። ይህ ዮሐንስ 14ን ያስታውሰናል።

**ዮሐንስ 14 (አዲሱ መ.ት)**

2 በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ ይህ ባይሆንማ ኖሮ እነግራችሁ ነበር፤ የምሄደውም ስፍራ ላዘጋጅላችሁ ነው። 3 ሄጄም ስፍራ ካዘጋጀሁላችሁ በኋላ፣ እኔ ባለሁበት እናንተም ከእኔ ጋር እንድትሆኑ ልወስዳችሁ ዳግመኛ እመጣለሁ።

ይህ ከሰርጉ ጋር ይመሳሰላል። በአይሁድ በአል መሰረት ባልየው ተመልሶ



GFX By: AD Graphics | +251916698510

መጥቶ ሚስቱን የሚወስድበትን የሰረጉን ቀን የሚገልጸው አባቱ ነው። ይህ ማለት ልጁ ቀኑን አያውቅም ማለት አይደለም። ነገርግን በባህሉ መሰረት ቀኑን ለሰዎች የሚገልፀው አባትየው ነው። ለምሳሌ እኔ ሄጄ ልጁን የሰርግህ ቀን መቼ ነው? ብለው። ይህንን የሚገልፀው አባቴ ነው የሚለው። ይህንንም ቀን ሚስቱ ስለማታውቅ፣ ባልየውም ስለማይነግራት በድንገት ነው የሚመጣው። እሷ ግን ተዘጋጅታ ነው የምትጠብቀው። መፅሐፍ ቅዱሳችን ላይ ጌታ ኢየሱስ እንደ ሙሽራ፣ ቤተክርስቲያን ደግሞ እንደ ሙሽራት ተገልፃለች። ኢየሱስ ዳግም የሚመጣበት ቀን ደግሞ እንደ ሰርግ ተገልጿል። ኢየሱስ እያለ ያለው እኔ ይህንን ነገር አልነግራችሁም እናንተ ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ እያለ ነው። ይህንን በይበልጥ ምዕራፍ 25 ላይ ያብራራዋል።

እስካሁን የተባለውን ይበልጥ የሚያብራራልን አንድ ወሳኝ ጥያቄ እንጠይቅ።

ጌታ ኢየሱስ በድንገት እንደሚመጣ ነው የሚናገረው። ታዲያ በድንገት ከሆነ መልክት መሰጠቱ ለምን አስፈለገ? እነዚህ ሁለቱ ነገሮች እንዴት ነው አብረው የሚሄዱት? ምልክት ከተሰጠ ድንገት መሆን የለበትም። ድንገት የሚሆን ከሆነ ምልክት አያስፈልገውም።

በእዛ ላይ ደግሞ ምልክቶቹ ከእዛ በፊት ያልነበሩ አይደሉም። ምልክቶቹ አለም ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ የነበሩ ናቸው። በማቴዎስ ውስት ከተጠቀሱት መካከል የተወሰኑትን እንኳን ብንመለከት ይህንን ለመረዳት ከባድ አይሆንም። ለምሳሌ ሐሰተኛ ነብያትን ብንመለከት በብሉይ ኪዳን ብዙ ነበሩ። ጦርና የጦር ወሬዎችን ትሰማላችሁ ይላል። ይህ ያልሆነበት ጊዜ ነበር እንዴ? ብሉይ ኪዳን እንዳለ የጦርነት ታሪክ ይበዛዋል። ከጦርነቱ ጋር ተያይዞ የሚመጣው ስደት፣ ረሃብ ድሮም ነበር። ስለዚህ ጦርነት በተነሳ ቁጥር ኢየሱስ ሊመጣ ነው ልንል ነው? በዘመን ፍፃሜ ይሆናሉ የተባሉት ምልክቶች በእየ ዘመኑ ነበሩ። ታዲያ ስለክርስቶስ ዳግም ምፅአት እንዴት እንደ ልዩ መልክት ተገለፀ?

ሮም በሚገዛበት ዘመን ሮም በአከባቢው የነበሩት መንግስት ቀጥ ለጥ ከድርጎ ይገዛ ነበር። ሮም ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዝቶ ሁሉንም እያስተዳደረ ነበር። በእዚያን ጊዜ ኮሽታ እንኳን አይሰማም ነበር።

**ፓክሳ ሮማና** ተብሎ ይጠራ ነበር። ሮም በሰላማ ማለት ነው። ሮም ሰላም ያሰፈነበት ዘመን ነበር። ጦርነት የሚባል ያልተሰማበት ዘመን ነበር።

ስለዚህ ጦርነት ይሰማል ማለቱ እንግዳ ነገር ነው። ኢየሱስ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ስለሚመጣው ጦርነት፣ ከጦርነቱ ጋር ተያይዞ ስለሚመጣው ረሃብ መናገሩ እንደ ልዩ ምልክት እንዲወሰድ አድርጎታል።

አይሁዶች በሮም መንግስት ያመፁበት እና የሮም መንግስት በአይሁድ ላይ ጦሩን እንዲያሰልፍ ያደረገበት ነው። ከእዚህ ጋር ተያይዞ ነው ኢየሩሳሌም ተቃጥሎ ምቅደሱ እንዲፈርስ የተደረገው።

የማቴዎስ ምዕራፍ 24 እና 25 በጣም ብዙ ትርጉሞች የተሰጡበት ክፍል እንደሆነ ተመልክተናል።

1ኛ, Preterists፦ ሁሉንም ትንቢቶች በ 70 AD ተፈፅመዋል ብለው ያምናሉ። የPreterists ዋና ሙግታቸው ቁጥር 34 ነው። ይህ ትውልድ አያልፍም የሚለው ነው። ስለዚህ ኢየሱስ የተናገራቸው ነገሮች የተፈፀሙት በእዚያው ዘመን የተፈፀመ እንጂ ለወደፊቱ የምንጠብቀው አይደለም። ይህንን ሲሉ ግን የማቴዎስ 24 ላይ ያለውን ብቻ ሳይሆን በሙሉ በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ ያለውንም ትንቢቶች ጨምሮ ነው።

2ኛ, Futurist (especially Dispensational Premillennialists ደግሞ፦ ማቴዎስ 24 ሙሉ በሙሉ ወደፊት የሚፈፀም ነው እንጂ እኛ ስንመለከተው ወደኋላ የተፈፀመ አንዳች ነገር የለም ይላሉ።

3ኛ, Partial Preterists ደግሞ ማቴዎስ 24 በ 70 AD የተፈፀሙትንም ይዟል ፣ ወደፊት የሚፈፀሙ ነገሮችንም ይዟል።

4ኛ, Double Fulfillment “Already–Not Yet” የሚሉት ነው። Already የተከናወነ ነው የሚሉት። በ AD 70 የተፈፀመው judgment ነው። Not yet የሚሉት ደግሞ final judgmentን ነው የሚያመለክተው ይላሉ። 70 AD shadow ሆኖ ሳለ final judgment የሚያብራራ ነው ይላሉ። ስለዚህ በአንድ ጊዜ ሁለት ነገሮችን እያወራ ነው ይላሉ።



GFX By: AD Graphics | +251916698510

የማቴዎስ 24ን ሙሉውን ሀሳብ መመልከት ባንችልም በዋናነት የምንመለከታቸው 7 ነገሮች ናቸው፡፡

1. የመንግስቱ ወንጌል ለአለም ሁሉ ይሰበካል፡፡
2. ታላቀ መከራ
3. ጨረቃ ኳክብት ይረግፋሉ የሚለው በቀጥታ የሚወሰድ አይደለም፡፡
4. ይህ ትውልድ አያልፍም
5. ሰማይና ምድር ያልፋሉ፡፡
6. ከአብ በቀር ልጅም ቢሆን አያውቅም
7. የአህዛብ ዘመን (ይህንን ቀጣይ ሳምንት እንመለከተዋወ)

ከላይ የተባለውን ይበልጥ የሚያብራራልን አንድ ወሳኝ ጥያቄ ጠይቀን ነበር፡፡

ጌታ ኢየሱስ በድንገት እንደሚመጣ ነው የሚናገረው፡፡ ታዲያ በድንገት ከሆነ መልክት መሰጠቱ ለምን አስፈለገ? እነዚህ ሁለቱ ነገሮች እንዴት ነው አብረው የሚሄዱት? ምልክት ከተሰጠ ድንገት መሆን የለበትም፡፡ ድንገት የሚሆን ከሆነ ምልክት አያስፈልገውም፡፡

በእዛ ላይ ደግሞ ምልክቶቹ ከእዛ በፊት ያልነበሩ አይደሉም፡፡ ምልክቶቹ አለም ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ የነበሩ ናቸው፡፡ በማቴዎስ ውስት ከተጠቀሱት መካከል የተወሰኑትን እንኳን ብንመለከት ይህንን ለመረዳት ከባድ አይሆንም፡፡ ለምሳሌ ሐሰተኛ ነብያትን ብንመለከት በብሉይ ኪዳን ብዙ ነበሩ፡፡ ጦርና የጦር ወሬዎችን ትሰማላችሁ ይላል፡፡ ይህ ያልሆነበት ጊዜ ነበር እንዴ? ብሉይ ኪዳን እንዳለ የጦርነት ታሪክ ይበዛዋል፡፡ ከጦርነቱጋር ተያይዞ የሚመጣው ስደት፣ ረሃብ ድሮም ነበር፡፡ ስለዚህ ጦርነት በተነሳ ቁጥር ኢየሱስ ሊመጣ ነው ልንል ነው? በዘመን ፍፃሜ ይሆናሉ የተባሉት ምልክቶች በእየ ዘመኑ ነበሩ፡፡ ታዲያ ስለክርስቶስ ዳግም ምፅአት እንዴት እንደ ልዩ መልክት ተገለፀ?

ሮም በሚገዛበት ዘመን ሮም በአከባቢው የነበሩት መንግስት ቀጥ ለጥ ከድርጎ ይገዛ ነበር፡፡ ሮም ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዝቶ ሁሉንም እያስተዳደረ ነበር፡፡ በእዚያን ጊዜ ኮሽታ እንኳን አይሰማም ነበር፡፡

<u>**ፓክሳ ሮማና**</u> ተብሎ ይጠራ ነበር፡፡ ሮም በሰላማ ማለት ነው፡፡ ሮም ሰላም ያሰፈነበት ዘመን ነበር፡፡ ጦርነት የሚባል ያልተሰማበት ዘመን ነበር፡፡

ስለዚህ ጦርነት ይሰማል ማለቱ እንግዳ ነገር ነው፡፡ ኢየሱስ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ስለሚመጣው ጦርነት፣ ከጦርነቱ ጋር ተያይዞ ስለሚመጣው ረሃብ መናነሩ እንደ ልዩ ምልክት እንዲወሰድ አድርጎታል፡፡

አይሁዶች በሮም መንግስት የመፁበት እና የሮም መንግስት በአይሁድ ላይ ጦሩን እንዲያሰልፍ ያደረገበት ነው፡፡ ከእዚህ ጋር ተያይዞ ነው ኢየሩሳሌም ተቃጥሎ ምቅደሱ እንዲፈርስ የተደረገው፡፡

## አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር

ራእይ 21፥1 (አዲሱ መ.ት)

> “ከዚህ በኋላ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር አየሁ፤ የመጀመሪያው ሰማይና የመጀመሪያዪቱ ምድር ዐልፈዋልና፤ ባሕርም ከእንግዲህ ወዲህ አይኖርም፡፡”

ይህ አድስ ሰማይና ምድር በኢሳይያስ 65፣ በ 2ኛ ጴጥሮስ 3 ላይ በሌሎች ክፍል ላይም ተጠቅሷል፡፡

<u>የሺኛው ዘመነ መንግስት ከተጠናቀቀ በኋላ የት ነው የምንኖረው</u>?

በአዲሱ ሰማይ እና በአዲሱ ምድር፡፡ ግን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ሲል ሌላ ግኡዝ ሰማይ፣ ሌላ ግኡዝ ምድር ማለት ነው? ወይን ከእዛ የተለየ ነው?

አንዳንዶች በሰማይ ይላሉ ሌሎች በምድር የሚሉ አሉ፡፡ ሁለቱም የእየራሳቸው የመከራከሪያ የሙግት ነጥቦች እና የሚያቀርቡት የመፅሐፍ ቅዱስ Textኦች አሉ፡፡

ትክክለኛው በሰማይ ሳይሆን በምድር መኖራችን ነው፡፡ ለእዚህም የመከራከሪያ ነጥቦችን አነሳለሁ፡፡


GFX By: AD Graphics | +251916698510

1ኛ, ቀድሞውንም ቢሆን የሰው ልጅ መኖሪያው ሰማይ ሳይሆን ምድር ነው

በዘፍጥረት ውስጥ እግዚአብሔር ሰውን ይፈጥራል ከእዚያ ወደ ምስራቅ ወደምትገኘው ኤደን ገነት ያኖረዋል፣ ከእዚያም ምድርን እንዲገዛ እና እንዲያስተዳድር ሀላፊነት ይሰጠዋል። እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው እና በምድር ሲያኖረው ሁሉም መልካም እንደሆነ ተመልክቷል።

2ኛ, ሰዎች በምድር እንደሚኖሩ መፅሐፍ ቅዱስ ይናገራል

መዝሙር ምዕራፍ 8 ላይ የሚጠቀሰ ሰው ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ላይ ያለው ሰው ነው። ማለትም ሰው አስቀድሞ ሲፈጠር የነበረበትን ሁኔታ የሚያወራ መፅሐፍ ነው። ዳዊት ከዘፍጥረት 1 ካለው ሰው ውጪ የሚጠቅሰውን ሰው አያውቀውም።

**መዝሙር 8 (አዲሱ መ.ት)**

1 እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ፤ ስምህ በምድር ሁሉ
ላይ ምንኛ ግርማዊ ነው! ክብርህ ከሰማያት በላይ፣
ከፍ ከፍ ብሎአል። 2 ከልጆችና ጡት ከሚጠቡ ሕፃናት
አፍ፣ ምስጋናን አዘጋጀህ፤ ከጠላትህ የተነሣ፣ ባላንጣንና
ቀመኛን ጸጥ ታሰኝ ዘንድ። 3 የጣቶችህን ሥራ፣ ሰማያትህን
ስመለከት፣ በስፍራቸው የኖርሃቸውን፣ ጨረቃንና ከዋክብትን
ሳይ፣ 4 በሐሳብህ ስፍራ ትሰጠው ዘንድ ሰው ምንድን
ነው? ትጠነቀቅለትም ዘንድ የሰው ልጅ ምንድን ነው?
5 ከመላእክት በጥቂት አሳነስኸው፤ የክብርንና የሞገስን
ዘውድ አቀዳጀኸው። 6 በእጆችህ ሥራ ላይ ሾምኸው፤
ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛህለት፤ 7 በጎችንና ላሞችን ሁሉ፣
የዱር አራዊትንም፣ 8 የሰማይ ወፎችንና፣ የባሕር ዓሦችን፣
በባሕር ውስጥ የሚርመሰመሱትንም ሁሉ አስገዛህለት። 9
እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ፤ ስምህ በምድር ሁሉ ላይ
ምንኛ ግርማዊ ነው!

ቁጥር 1 ላይ ቃላት በጣረው መልኩ ስለ እግዚአብሔር Majesty ይናገራል። ምንኛ ግርማዊ ነው፣ ከፍ ከፍ ብሎአል የሚሉ ቃላት እየተጠቀመ እግዚአብሔር ወደር የሌለው በግርማው አስገራሚ አምላክ መሆኑን ያመለክታል።

> 2 ከልጆችና ጡት ከሚጠቡ ሕፃናት አፍ፣ ምስጋናን አዘጋጀህ፤ ከጠላትህ የተነሣ፣ ባላንጣንና ቀመኛን ጸጥ ታሰኝ ዘንድ።

በግርማ እና ሞገስህ Already አንተ እኮ እጅግ የከበርክ ነህ ብሎት ነበር በቁጥር 1። አሁን ደግሞ ከህፃናት ምስጋና ለመቀበል መምረጥህ እጅግ አስገራሚ ነው እያለ ይደነቃል። ህፃናት የሚለው የሰው ፍጥረትን ለመግለጽ ነው።

ለምንድን ከሰዎች መስጋናን መቀበል አስገራሚ ነገር የሆነው? ይህንን በቁጥር ሶስት ይነግረናል።

> 3 የጣቶችህን ሥራ፣ ሰማያትህን ስመለከት፣ በስፍራቸው የኖርሃቸውን፣ ጨረቃንና ከዋክብትን ሳይ፣ 4 በሐሳብህ ስፍራ ትሰጠው ዘንድ ሰው ምንድን ነው? ትጠነቀቅለትም ዘንድ የሰው ልጅ ምንድን ነው?

ቁጥር 3 ሌሎች ፍጥረትን ስላየ ነው የተገረመው። በጣም ግዙፍ የሆነውን ፍጥረት ተመልክቼ በንፅፅር ሰውን ስመለከት ታስበው ዘንድ ሰው ምንድነው የሚለው ጥያቄ በዳዊት ላይ ጫረበት።

> 5 ከመላእክት በጥቂት አሳነስኸው፤ የክብርንና የሞገስን ዘውድ አቀዳጀኸው።

መላዕክት የሚለው የዕብራይስጡ ቃል ኤሎሂም ነው። ይህ ቃል ለመላዕክትም ሆነ ለአምላክ ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው። ስለዚህ አምላክ እንበለው ወይንስ ሰው? አምላክ ነው የሚሉት ንፅፅሩ አምላክ ፍጥረት እና ሰው ስለሆነ ኤሎሂም የሚለውም አምላክ ለሚለው መሆን አለበት ይላሉ። እኔ ግን መላእክት ለሚለው ቢገባ የተሻለ ነው።



GFX By: AD Graphics | +251916698510

ደግሞም የሰባ ሊቃናቱ ትርጉም <u>**ለጥቂት ጊዜ**</u> ብሎ ነው የተረጎሙት፡፡ ለጥቂት ጊዜ የሚለው የሰው ልጅ ወደ ነበረበት አገዛዝ የሚመለስበት ጊዜ እንዳለም አቅጣጫ የሚጠቁም ነው፡፡ ይህ የውድቀት ዘመን የሚያበቃበትና ሰው ወደ ክብሩ የሚመለስበት ዘመን እንደሚመጣ ዳዊት ተረድቷል፡፡ ነገርግን አማኞች አሁን የሚጠብቃቸው ክብር ቀድሞ ከነበረው ክብር እጅግ ከፍ ያለ ነው፡፡ እግዚአብሔር አማኞችን በክርስቶስ በኩል ሲያከብራቸው አዳም ቀድሞ ወደነበረበት ሁኔታ ብቻ አልመለሰውም፡፡ አዳም ቢታዘዝ ኖሮ የሚያገኘውን ሽልማት ነው የሰጣቸው፡፡ ይህም በክርስቶስ መታዘዝ መክንያት ነው፡፡

ራእይ 2፥7 (አዲሱ መ.ት)

> “መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚናገረውን፣ ጆሮ ያለው ይስማ፤ ድል ለሚነሣ በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ አደርገዋለሁ፡፡”

ሌላኛው 2ኛ ጴጥሮስ ላይ ያለው ነው

2ኛ የጴጥሮስ መልእክት 3:6-7 (NASV)

> 6 በዚያን ጊዜ የነበረው ዓለም በውሃ ተጥለቅልቆ ጠፋ፡፡
> 7 በዚያው ቃል ደግሞ አሁን ያሉት ሰማያትና ምድር፣ ኀጢአተኞች እስከሚጠፉበት እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ለእሳት ተጠብቀዋል፡፡

እዚህ ክፍል ላይ አንድ ጥያቄ እንጠይቅ፡፡ በኖህ ዘመን የነበሩ አለም ተራራ እና ሜዳው ሸንተረሩ ጠፍቶ አዲስ አለም ተፈጥሯል? ፍፁም፡፡ እግዚአብሔር ከኖህ ዘመን በፊት የነበሩ ኃጢአተኞችን ነው ያጠፋቸው፡፡ በእዚህ ቃል አሁን ያሉቱ ሰማይና ምድር ይጠፋሉ ሲል ይህ የሚታየው ሰማይ እና ምድር ሊሆን አይችልም፡፡

3ኛ, <u>እግዚአብሔር ከፍጥረት ስራው ስላረፈ ሌላ የሚፈጥረው ሰማይና ምድር የለም</u>

የዘፍጥረት መፅሐፍ የሚነግረን እግዚአብሔር ሊፈጠሩ የተገባቸውን ፍጥረቶ ፈጥሮ ከመፍጠር ስራው አርፏል፡፡

በእርግጥ እግዚአብሔር ከመፍጠር ስራው ቢያርፍም የፍጥረቱ ከመንከባከብ፣ ከመመመገብ፣ እና ኃጢአት ከገባበት ጊዜ አንስቶ ደግሞ ፍጥረቱ ከማደስ አላረፈም፡፡

ነገርግን እግዚአብሔር ሌላ ሰማይ እና ሌላ ምድር የሚፈጥር ከሆነ ዘፍጥረት ላይ ካለው ሀሳብ ጋር ይጋጫል፡፡

4ኛ, <u>ሰማይና ምድር የሚጠፋ ከሆነ እግዚአብሔር ተሸናፊ ነው</u>

እስቲ እናስብ ሰማይና ምድር ምን አደረጉና ነው የሚጠፉት? ሰው ነው ኃጢአተኛ የሆነው፡፡ ተራራ ሜዳ ሸንተረሩ ኃጢአት አይሰራም፣ በኃጢአት ተፅዕኖ ስር አይወድቅም፡፡ እግዚአብሔር መልካም እንደሆነ ያየውን ፍጥረተ ነው ማስወገድ ያለበት? ወይንስ ኃጢአትን? ኃጢአትን ነው ማስወገድ ያለበት አሰንጂ ፍጥረቱን አይደለም፡፡ ምክንያቱም ኃጢአት የእግዚአብሔር ፍጥረት ስላልሆነ፡፡

<u>**ታዲያ በሰማይ ነው የሚንኖረው የሚሉ textኦችን እንዴት እንመለከታለን**</u>?

እሱ ሥነ-አፈታት(Hermeneutics) ጉዳይ ነው፡፡

ማቴዎስ 24:35

> “ሰማይና ምድር ያልፋሉ፤ ቃሌ ግን ፈጽሞ አያልፍም፡፡”

ሰማይና ምድር ሲል የትኛው ሰማይ እና ምድር? ይህ ጉኡዞ ሰማይ እና ምድር፣ ቀና ስንል የሚታየውን ሰማይ በእግራችን የምንረግጠውን ምድር ነው? ወይንስ ሌላ ትርጉም አለው? ሰማይና ምድር ሲል አንድን Kingdom ለመግለጥ የሚጠቀሙበት ቋንቋ ነው፡፡ የእዚህ የማቴዎስ 24 Context ደግሞ ስለ እስራኤል መንግስት ማለፍ ነው የሚናገረው፡፡ በሙሴ ስርአት ሲተዳደር የነበረውን ብሉይ ኪዳናዊውን መንግስት ነው የሚያወራው፡፡ በአጭሩ ብሉይ ኪዳን አልፎ በአዲሱ ኪዳን እደሚተካ ነው የሚያወራው፡፡

በእዚያን ዘመን የነበሩ በ<u>**መሶፖታሚያ**</u> አከባቢ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ይጠቀሙበት



GFX By: AD Graphics | +251916698510

የነበረው የአነጋገር ስልት ነው፡፡ሰማይ እና ምድር የሚለው የእስራኤልን ህዝብ ለመግለጽ መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

**ኦሪት ዘዳግም 32:1 (NASV)**

1 ሰማያት ሆይ፤ አድምጡ፤ እኔም እናገራለሁ፤ ምድር ሆይ፤
አንቺም የአፌን ቃል ስሚ፡፡

**ትንቢተ ኢሳይያስ 1:2 (NASV)**

2 ሰማያት ሆይ፤ ስሙ! ምድር ሆይ፤ አድምጪ! እግዚአብሔር
እንዲህ ሲል ተናግሯልና፤ “ልጆች ወለድሁ፣ አሳደግኋቸውም፤
እነርሱ ግን ዐመፁብኝ፡፡

ሌላኛው ፦

**የሐንስ 14:1-3 የሐንስ 14 (አዲሱ መ.ት)**

1 “ልባችሁ አይጨነቅ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፤ በእኔም
ደግሞ እመኑ፡፡
2 በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ ይህ
ባይሆንማ ኖሮ እነግራችሁ ነበር፤ የምሄደውም ስፍራ
ላዘጋጅላችሁ ነው፡፡
3 ሄጄም ስፍራ ካዘጋጀሁላችሁ በኋላ፣
እኔ ባለሁበት እናንተም ከእኔ ጋር እንድትሆኑ ልወስዳችሁ
ዳግመኛ እመጣለሁ፡፡
4 እኔ ወደምሄድበትም ስፍራ
የሚያደርሰውን መንገድ ታውቃላችሁ፡፡”

ይህንን ለመረዳት ከምዕራፍ 13 ጀምሮ ያለውን መረዳት ወሳኝ ነው፡፡ ኢየሱስ እሄዳለሁ ሲል ወዴት ነው እሄዳለሁ የሚለው?

**የሐንስ 13 (አዲሱ መ.ት)**

36 ስምዖን ጴጥሮስ፣ “ጌታ ሆይ፤ የምትሄደው ወዴት
ነው?” አለው፡፡ ኢየሱስም፣ “ወደምሄድበት አሁን ልትከተለኝ
አትችልም፤ ኋላ ግን ትከተለኛለህ” ሲል መለሰለት፡፡
37 ጴጥሮስም፣ “ጌታ ሆይ፤ አሁን ልከተልህ የማልችለው
ለምንድን ነው? ስለ አንተ ሕይወቴንም ቢሆን አሳልፌ
እሰጣለሁ” አለው፡፡
38 ኢየሱስም፣ እንዲህ ሲል መለሰ፤
“ሕይወትህን በርግጥ ለእኔ አሳልፈህ ትሰጣለህን? እውነት
እልሃለሁ፤ ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ፡፡”

ኢየሱስ እሄዳለሁ ሲል እዚህ ጋር ሞቱን ነው እየተናገረ ያለው፡፡ ስፍራ አዘጋጃለሁ የሚለው ደግሞ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቅዱስ መቅደስ መሆናችን ነው፡፡

**የሐንስ 14 (አዲሱ መ.ት)**

23 ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ “የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን
ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል፤ ወደ እርሱ እንመጣለን፤
ከእርሱም ጋር እንኖራለን፡፡

ሌላኛው 2ኛ ቆሮንቶስ 5 ላይ ያለው ቃል ነው፡፡

**2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 5:1-4 (NASV)**

1 መኖሪያችን የሆነው ምድራዊ ድንኳን ቢፈርስም፣ በሰው
እጅ ያልተሠራ ነገር ግን ከእግዚአብሔር የሆነ ዘላለማዊ
ቤት በሰማይ እንዳለን እናውቃለን፡፡

ይህንን ክፍል ቀጥር አንድ ላይ ብቻ አንብቦ የቆመ ሰው ሀሳቡን መረዳት አይችልም፡፡ ከላይ አስቀድሞ የተናገረውን እና ቀጥሎ ያለውን ቀጥር መመልከት ይኖርበታል፡፡ ክፍሉ እያወራ ያለው ሰማይ የሆነ ስለሚሰራ እቤት ሳይሆን የትንሳኤን አካል ስለመልበሳችን ነው፡፡ ይህንን አንድ ቀጥር እንኳን ወደታች ብንመለከት እና ምዕራፍ 4ትን ብንመለከት እንረዳለን፡፡

2 እስከዚያው ግን የሰማዩን መኖሪያችንን ለመልበስ
እየናፈቅን እንቃትታለን፤
3 በርግጥ ከለበስነው ራቍታችንን
ሆነን አንገኝም፡፡
4 በዚህ ድንኳን እስካለን ድረስ ከብዶን
እንቃትታለን፤ ምክንያቱም ሟች የሆነው በሕይወት
እንዲዋጥ ሰማያዊውን መኖሪያችንን ልንለብስ እንጂ
ልንገፈፍ አንፈልግም፡፡



GFX By: AD Graphics | +251916698510

**2ኛ ቆሮንቶስ 4:7,10-11,14,17-18 (NASV)**

7 ነገር ግን ይህ እጅግ ታላቅ ኀይል ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ
አለመሆኑን ለማሳየት፣ ይህ የከበረ ነገር በሸክላ ዕቃ ውስጥ
አለን፡፡........10 የኢየሱስ ሕይወት በሰውነታችን እንዲገለጥ፣
የኢየሱስን ሞት ዘወትር በሰውነታችን ተሸክመን እንዞራለን፡፡
11 የኢየሱስ ሕይወት ሟች በሆነው ሥጋችን እንዲገለጥ፣
እኛ ሕያዋን የሆንን ሁልጊዜ ስለ ኢየሱስ ለሞት ዐልፈን
እንሰጣለንና፡፡.....14 ምክንያቱም ጌታ ኢየሱስን ከሙታን
ያስነሣው እኛንም ደግሞ ከኢየሱስ ጋር አስነሥቶ ከእናንተ
ጋር በፊቱ እንደሚያቀርበን እናውቃለን፡፡.....17 ምክንያቱም
ቀላልና ጊዜያዊ የሆነው መከራችን ወደር የማይገኝለት
ዘላለማዊ ክብር ያስገኝልናል፡፡ 18 ስለዚህ ዐይናችን
የሚያተኵረው በሚታየው ነገር ላይ ሳይሆን በማይታየው
ላይ ነው፤ የሚታየው ጊዜያዊ ነውና፤ የማይታየው ግን
ዘላለማዊ ነው፡፡

ሌላኛው ፊልጵስዩስ 3:20 ላይ ያለው ነው፡፡

**ፊልጵስዩስ 3:20-21 (NASV)**

20 እኛ ግን አገራችን በሰማይ ነው፤ ከዚያ የሚመጣውንም
አዳኝ፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በናፍቆት እንጠባበቃለን፤
21 እርሱም ሁሉን ለራሱ ባስገዛበት ኀይል፣ ክቡር ሥጋውን
እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል፡፡

ጳውሎስ እዚህ ጋር በዘመኑ ሲጠቀሙ የነበረውን አይነት አባባል ነው እየተጠቀመ ያለው፡፡ በዘመኑ የነበሩት ሮማዊያን የተለመደ አባባል አላቸው፡፡ እኛ ሀገራችን በሮም ነው፡፡ የምንኖረው በፊልጵስዩስ ነው ይላሉ፡፡ ይህንን ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? የሮምን ስርአተ መንግስት በፊልጵስዩስ እንገነባለን እያሉ ነው፡፡ ጳውሎስ እያለ ያለው የሰማይ አገዛዝ በምድር ላይ ይሆናል እያለ ነው፡፡

ደግሞም ክፍሉን በጥንቃቄ ከተመለከትን እኛ ወደሰማይ እንሄዳለን ሳይሆን የሚለው አዳኙ ከሰማይ ይመጣል ነው የሚለው፡፡ ወዴት ነው የሚመጣው? እኛ ወዳለንበት ምድር ነው የሚመጣው፡፡

ሌላኛው ራዕይ 21:1 ላይ ያለው ነው፡፡

**ራእይ 21፥1 (አዲሱ መ.ት)**

“ከዚህ በኋላ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር አየሁ፤ የመጀመሪያው ሰማይና የመጀመሪያዪቱ ምድር ዐልፈዋልና፤ ባሕርም ከእንግዲህ ወዲህ አይኖርም፡፡”

አዲስ እየተባለ ያለው ከቀድሞው አንፃር ነው፡፡ በቀድሞ ዘመን ያልነበረ አዲስ ስርአት ማለት ነው፡፡

ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው ሲል ውጫዊ ገፅታውምንም የሚለወጥ ነገር የለም፡፡ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደገና የሚፈጠር ከሆነ እና እኛ ሰማይ የምንኖር ከሆነ የመድር የመፈጠሩ አስፈላጊነቱ ታዲያ ምኑ ጋር ነው? ፣ በምድርስ ማን ሊኖር ነው? አዲስ የሚለው የግሪክ ቃል ካይኖስ የሚል ነው፡፡ አንዳንዶች መታደስን እንጂ ሙሉ በሙሉ መወገድን አይደለም ይላሉ፡፡ በእርግጥ ሀሳቡ ልክ ነው፡፡

እግዚአብሔር ፍጥረቱን የሚያድስ እንጂ የሚያጠፋ አይደለም፡፡

**ሮሜ 8 (አዲሱ መ.ት)**

19 ፍጥረት ሁሉ የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ በናፍቆት
ይጠባበቃል፡፡ 20 ፍጥረት ሁሉ ለከንቱነት ተዳርጎአል፤ ይኸውም
በራሱ ምርጫ ሳይሆን፣ ለተስፋ እንዲገዛ ካደረገው ከፈቃዱ
የተነሣ ነው፡፡ 21 ይህም ፍጥረት ራሱ ከመበስበስ ባርነት ነጻ
ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደ ሆነው ወደ ከበረው
ነጻነት እንዲደርስ ነው፡፡ 22 እስከ አሁን ድረስ ፍጥረት ሁሉ
በምጥ ጊዜ እንዳለው ሥቃይ በመቃተት ላይ እንደሚገኝ
እናውቃለን፡፡ 23 እርሱ ብቻ ሳይሆን፣ የመጀመሪያውን


GFX By: AD Graphics | +251916698510

የመንፈስ ፍሬ ያገኘን እኛ ራሳችን የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነታችንን በናፍቆት እየተጠባበቅን በውስጣችን እንቃትታለን፡፡

ኢሳይያስ 65 ላይ ስለ አዲስ ሰማይና ስለ አዲስ ምድር አተነግሮል፡፡

ትንቢተ ኢሳይያስ 65:17-18 (NASV)

17 “እነሆ፤ እኔ፣ አዲስ ሰማያትንና አዲስ ምድርን እፈጥራለሁ፤
ያለፉት ነገሮች አይታሰቡም፤ አይታወሱም፡፡

እዚህ ቁጥር ላይ አንዳንድ ሰዎች የእዚህ ሰማይና ምድር መወገድ እና የሚታየው ሰማይና ምድር መምጣት ነው ይላሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ የ ሺኛው ዘመነ መንግስት ነው ይላሉ፡፡ ትልቁ ችግር ሰው ቁጥር 17ትን እንጂ ቁጥር 18ን አያነብም፡፡

18 ነገር ግን በምፈጥረው፣ ደስ ይበላችሁ፤ ለዘላለም
ሐሤት አድርጉ፡፡ ኢየሩሳሌምን ለደስታ፣ ሕዝቧን ለሐሤት
እፈጥራለሁና፡፡

ወደታች እያነበብን ስንሄድ የሚሞቱ ሰዎች ያሉበት፣ የማያምኑ ሰዎች ያሉበት ነው፡፡ በጠቅላላ ይህ ክፍል ስለ አዲሱ ኪዳን ነው የሚያወራው፡፡

ሌላኛው ዕብራውያን 1:11 ላይ ያለው ነው፡፡

ዕብራውያን 1 (አዲሱ መ.ት)

10 ደግሞም እንዲህ ይላል፤ “ጌታ ሆይ፤ አንተ በመጀመሪያ
የምድርን መሠረት አኖርህ፤ ሰማያትም የእጆችህ ሥራ
ናቸው፡፡ 11 እነርሱ ይጠፋሉ፤ አንተ ግን ጸንተህ ትኖራለህ፤
ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃሉ፤ 12 እንደ መጐናጸፊያ
ትጠቀልላቸዋለህ፤ እንደ ልብስም ይለወጣሉ፡፡ አንተ ግን
ያው አንተ ነህ፤ ዘመንህም ፍጻሜ የለውም፡፡”

ይህንን ዕብራውያን ስንማር ተመልክተነዋል፡፡ እዛ ላይ ሙሉውን ማብራሪያ መመልከት ይቻላል፡፡ የዕብራውያን መፅሐፍ ሀሳብ ንፅፅሩ የሰማይና የምድር መጥፋትና የክርስቶስ አለመጥፋት ሳይሆን የሰማይና የምድር መለወጥ ከክርስቶስ አይለወጤነት ጋር ተያይዞ የቀረበ ነው፡፡

አንዳንድ ሰዎች እኛ በምድር ነው የምንኖረው ስንል ጆሆቫ ዊትነስ ናችሁ ይሉናል፡፡ ይህ እና የምንለውም ጆሆቫዎች የሚሉትንም አለመረዳት ነው፡፡ ጆሆቫዎች ምድር ገነት ናት ሲሉ እና እኛ በምድር እንኖራለን ስንል ልዩነት አለ፡፡ እነሱ ክርስቶስ መጥቷል፣ አሁን ምድር ገነት ስለሆነች እያለማናት እንመጣለን ነው የሚለት፡፡ እኛ ደግሞ ክርስቶስ እንደ ሚመጣ እናምናለን ፣ አሁን ያለንበት አለም የተበለሸ አለም ፣ ኢየሱስ ሲመጣ ይህንን የተበላሸውን አለም ያድሳል፡፡

## <u>እንዴት</u>?

ኃጢአትን፣ ኃጢአተኞችን፣ ሰይጣንን እና Sinful Natureን ያስወግዳል፡፡ ከኢየሱስ ጋር መሆናችን እንጂ ዋናው ነገር ሰማይ ወይንም ምድር መሆናችን አይደለም ዋናው ነገር፡፡ አንዳንዶች ወናው ነገር ከኢየሱስ ጋር መሆኑ እንዳልሆነላቸው የምናውቀው ምድር ነው የምንኖረው ስንል ይደነግጣሉ፡፡ ለእነሱ የሆነ ቆንጆ ቦታ፣ የወርቅ ረጅም መንገድ ከእዛ ነጫጭ የለበሱ መላዕክት ቆመው ሲመለከቷቸው ነው የሚስሉት፡፡ አንድም ቦታ መፅሐፍ ቅዱስ ስለ አለም ፍፃሜ ሲናገር ስለ ቁሳዊው አለም መወገድ አይናገርም፡፡ የሚወገደው በዘመን ውስጥ ስላለው ስርአት ነው፡፡ ስለዚህ ዘመን እንጂ መጨረሻ ያለው ሰማይና ምድር አይደለም፡፡



GFX By: AD Graphics | +251916698510

# ማጠቃለያ

የክርስትና ትምህርት የሰው ሕይወት በሥጋ ሞት እንደማይቋረጥ ያረጋግጣል፡፡ ይልቁንም እያንዳንዱ ሰው ለፍርድ በእግዚአብሔር ፊት ይቆማል፡፡ ክርስቶስን ያመኑት በእግዚአብሔር ፊት የዘላለም ሕይወት ተስፋ አላቸው፡፡ እርሱን የካዱት ሰዎች ከእግዚአብሔር ፀጋ ተለይተው በዘለዓለም የእግዚአብሔር ቁጣ ውስጥ ይኖራሉ፡፡

የእነዚህን እውነታዎች ዝርዝር ሁኔታን በተመለከተ በክርስቲያናዊ ትውፊቶች መካከል ትርጓሜዎች ቢለያዩም ፤ በዋናወቀቹ እውነታ ላይ ግን የጋራ ስምምነት አላቸው፡፡

የክርስቶስ ዳግም መምጣት እና የፍጥረት መታደስ እውነታ ለመከራ እና ለቅዱስ ህይወት መነሳሳትን ይሰጣል፡፡ አማኞች ድካማቸው ከንቱ እንዳልሆነ አውቀው ወደ ንቁነት እና ዝግጁ ወደ ሆነ ህይወት እንዲገቡ በእግዚአብሔር ተልዕኮ ተሰጥቷቸዋል፡፡

አለም ያለ አላማ ወደ ጥፋት እየገሰገሰች ሳይሆን በእግዚአብሔር ሉዓላዊ እቅድ ወደ ተሃድሶ እያመራች ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገሩ ትንቢቶች በመሉ በተፃፉበት እውነት በርግጥ ፍጻሜን ያገኛሉ፡፡እግዚአብሔር ዘፍጥረትን ፈጥሮ የተወ ሳይሆን በሉዓላዊነቱ እያስተዳደረ የሚመግብ ነው፡፡በመሆኑም በፍጥረት ታሪክ የተከናወነው ሆነ ወደፊት የሚከናወኑ ነገሮች በቅዱሳት መጻሕፍት በግልጽ ተቀምጠው ይገኛሉ፡፡ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት እና በአሁን መካከል የጊዜ÷ የባህል÷ የቋንቋ እና ሌሎችም ልዩነቶች ስላሉ በስነ አፈታት በመታገዝ በጥንቃቄ ልንመለከት ያስፈልገናል፡፡